12ኛ ጥያቄ፥ አይሁድ የነበሩበትን ታሪካዊ ሁኔታ ማወቅ ነቢያትንና እነርሱ ያመጡአቸውን ልዩ መልእክቶች አስፈላጊነት ለመረዳት ምን ያህል የሚጠቅም ይመስልሃል?

6. በዚያ ክፍል ውስጥ ነቢዩ ለአይሁድ ሊያስተምር የሞከረውን ዋናውን መልእክት ለማግኘት ሞክር። ትንቢት የሚሰጥበት ዋና ምክንያት ስለ ወደፊቱ ሁኔታ ለሰዎች ለመናገር አይደለም። ይልቁንም ሰዎችን ለማበረታታት፥ ለመገሠጽና ለማስጠንቀቅ ነበር፤ የክፍሉ ዋና መልእክት ይህ ነው። ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረናል? ስለተቀደሰ አኗኗር ምን ያስተምረናል? እግዚአብሔር ፍርድን ስለሚያመጣበት መንገድ ምን ያስተምረናል?

ትንቢቱን ለመረዳት በመሞከር አሳብህ ከመበታተኑ በፊት፥ መልእክቱን ለመረዳትህ እርግጠኛ ሁን። ትንቢት ሁልጊዜ የሚሰጠው በዚያን ወቅት የነበሩትን ሰዎች አኗኗርና አስተሳሰብ ለመለወጥ ነበር። ብዙ ሰዎች ወደፊት የሚሆነውን ነገር እንዲያውቁ ተብሎ የሚሰጥ አልነበረም። የክፍሉ ዋና ትምህርት ብዙ ጊዜ በዚህ ዘመን ላለች ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ የሆነ መልእክት ነው። ስለዚህ በነቢዩ በኩል እግዚአብሔር ለዚያ ዘመን ሰዎች እንዲደርስ የፈለገው መልእክት ምን እንደሆነ በጥንቃቄ ተመልከት፤ እንዲሁም ለአንተና ለቤተ ክርስቲያንህ እንዲደርስ የፈለገው መልእክት ምን እንደሆነ በጥንቃቄ ተመልከት። ለምሳሌ፦ ነቢያት እግዚአብሔር ወደፊት ሊያደርገው ስለሚፈልገው ነገር የተናገሩበት ዋና ምክንያት በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ታሪካቸውን የሚቆጣጠረውንና በቅድስና የሚኖረውን እግዚአብሔርን በማክበር ይኖሩ ዘንድ ነበር። ነቢያት እግዚአብሔር እንዲከበር ይፈልጉ ነበር። በተለይ ደግሞ ትንቢቶቹ በሚፈጸሙበት ጊዜ የነበሩ ሰዎች እንዲያከብሩት ይፈልጉ ነበር።

7. የነቢያትን መልእክት አይሁድ ለቃል ኪዳኑ ቢታዘዙ ወይም ባይታዘዙ ስለሚሆነው ነገር ከተጻፈባቸው ከአሪት ዘሌዋውያን፥ ዘጎልቁና ዘዳግም ጋር አወዳድር። ግንኙነታቸው እንዴት ነው? እንዲሁም በታሪክ ውስጥ በኋላ ከታዩት፥ በተለይም ደግሞ በአዲስ ኪዳን ከተገለጡት ትንቢቶች ጋር አወዳድር። እነዚህ ባመዛኙ ቀደም ሲል የተነገረውን ትንቢት ለመረዳትም ይጠቅሙናል። ጊዜው እያለፈ በሄደ

መጠን የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠን መረጃ እየጨመረ መሄዱን አስታውስ። ስለሆነም እውቀት በኋለኞቹ መጻሕፍት የበለጠ እየጨመረ መሄዱን ተመልከት።

8. ያ ክፍል የያዘው ትንቢት ምን ዓይነት እንደሆነ ወስን። ነቢያት ብዙ ጊዜ የጻፉባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፡-

ሀ. በክስ መልክ የቀረበ መልእክት፡- በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የፍርድ ቤት ችሎት በመካሄድ ላይ እያለ የቀረቡ የሚመስሉ ብዙ ክፍሎች አሉ። እግዚአብሔር እስራኤላውያን የገቡትን ቃል ኪዳን እንዳፈረሱ የሚጠይቅ ዳኛና ዐቃቤ ሕግ ነው። አንዳንድ ጊዜ ፍጥረት ምስክር ወይም ታዛቢ ሆኖ ተጠቅሶአል። እስራኤላውያን ደግሞ ተከሳሾችም ጠበቆችም ነበሩ (ለምሳሌ፡- ኢሳይያስ 3፡13-26)

ለ. ፍርድንና ዋይታን የሚያውጅ መልእክት፡- ብዙ ጊዜ እነዚህ ክፍሎች «ወዮ» የሚለውን ቃል የያዙ ናቸው። በእነዚህ ክፍሎች ብዙ ጊዜ ነቢዩ በመምጣት ላይ ያለውን ጥፋት፥ የጥፋቱን ምክንያቶችና የጥፋቱን ዓይነት የሚያመለክቱ ነገሮችን ይናገራል (ለምሳሌ፡- ዕንባቆም 2፡6-8፤ ኢሳይያስ 5፡8-23)።

ሐ. ሊመጣ ስላለው በረከት የሚያውጅ መልእክት፡- የነቢያት አብዛኛው መልእክት ፍርድና ዋይታ ያለበት ቢሆንም፥ በእያንዳንዱ ነቢይ መልእክት ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ተበታትኖ ያለ የበረከት ተስፋ እናገኛለን። እነዚህ በረከቶች ብዙውን ጊዜ «በዚያን ቀን» የሚል ሐረግ አለባቸው። ይህም በረከቱ የሚመጣበትን ያልተወሰነ ጊዜ የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ፤- አሞጽ 9፡11-15፤ ሆሴዕ 2፡16-23)።

መ. ስለ ወደፊት ታሪካዊ ድርጊቶች ለመናገር ከፍተኛ ተምሳሌታዊ መግለጫዎችን የሚጠቀሙ ትንቢቶች፡- እነዚህ ክፍሎች ብዙ ጊዜ የአንድን ነገር፥ በተለይም የዓለምን ፍጹም ውድመት የሚያመለክቱ («አፖካሊፕቲክ») ክፍሎች በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ ክፍሎች ራእይና መላእክት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱባቸው ብዙ ተምሳሌቶች አሏቸው። (ለምሳሌ፡- ራእይ 4-22፤ ዳን.

7-12፤ ዘካርያስ 1፡8-14)። እነዚህ ክፍሎች ለመተርጐም እጅግ አስቸጋሪ ስለሆኑ፥ ግምታችን በትርጒሙ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

9. የነቢዩ መልእክት ነቢዩ ይኖርበት ለነበረው ዘመን ብቻ የተነገረ ወይም ስለ ወደፊቱ ዘመን ጭምር መሆን አለመሆኑን ወስን። እዚህ ላይ ነቢዩ ሕዝቡን እየወነጀለ፥ እግዚአብሔር ለምን እንደሚፈርድባቸው እየነገራቸው ነው ወይስ በኃጢአታቸው ምክንያት ወደፊት ምን እንደሚድርስባቸው እያስጠነቀቃቸው ነው ያለው?

10. ስለ መጪው ጊዜ የሚናገሩትን ትንቢቶች በምትመለከትበት ጊዜ፥ የተነገሩት ጉዳዮች ተፈጽመው እንደሆነ ወይም ገና ወደፊት የሚፈጸሙ ስለ መሆናቸው ወስን። ቀደም ሲል እንደገለጽነው፥ በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹ ትንበያዎች ተፈጽመዋል። በአሦራውያን ወይም በባቢሎናውያን አማካይነት በተከናወነው ምርኮ ወይም እስራኤላውያን ከምርኮ በተመለሱበት ጊዜ ተፈጽመዋል። እንዲሁም አብዛኛዎቹ በክርስቶስ መጀመሪያ መምጫ ጊዜ ተፈጽመዋል።

11. ወደፊት ስለሚፈጸሙ ነገሮች በግልጽ ስለሚናገሩ ክፍሎች ልናስታውሳቸውና ከሌሎቹ ልንለያቸው የሚያስፈልጉን አራት ዓይነት ትንቢቶች አሉ፤ እነርሱም፡-

ሀ. በቀጥታ የተፈጸሙ ቀጥተኛ ትንቢቶች፡- በእነዚህ ዓይነቶቹ ትንቢቶች ፍጻሜው የተለየን ድርጊት የሚያመለክት ሆኖ፥ ልክ እንደ ትንቢቱ ይፈጸማል (ለምሳሌ፡- ሚክ. 5፡2)።

ለ. ተምሳሌታዊ ትንቢቶች ሆነው በተምሳሌነት የተፈጸሙ፡- የእነዚህ ዓይነቶቹ ትንቢቶች ብዙ ጊዜ የሚነገሩት ነቢያቱ ይኖሩበት በነበረው ዘመን ስለተከናወኑት ነገሮች ወይም በቡራይ ኪዳን ውስጥ ስለተፈጸሙት ነገሮች ነው። ይሁን እንጂ በአንዳንድ መንገዶች በአዲስ ኪዳን የተፈጸሙ ድርጊቶችን በተምሳሌት የሚያሳዩ ናቸው (ለምሳሌ፡- ዘካርያስ 11፡12-13፤ ማቴዎስ 26፡14-15፤ 27፡3-10፤ ሆሴዕ. 11፡1፤ ማቴዎስ 2፡14-15)። ብዙውን ጊዜ እነዚህን ነገሮች መረዳት የሚቻለው

ስለ ክርስቶስ የሚናገሩ መሆናቸውን አዲስ ኪዳን በማረጋገጡ ነው። ከአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የምንለይበት ነገር ቢኖር የትኞቹ ትንቢቶች በተምሳሌታዊ ሁኔታ ወደ ክርስቶስ እንደሚያመለክቱ የሚነግረን መንፈስ ቅዱስ ስለሌለን ትንቢቶችን ከመጠን በላይ ጠልቀን ከማንበብ ልንቆጠብ ይገባል።

ሐ. ሁለት ትርጉም የነበራቸው ትንቢቶች፡- አንዳንድ ትንቢቶች ለእስራኤላውያን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ስለሚፈጸሙባቸው ነገሮች የተሰጡ ቢሆኑም እንኳ ከብዙ ዓመታት በኋላ በተለይም በዘመናት መጨረሻ የሚፈጸሙ ነገሮች ተምሳሌቶች ናቸው። (ለምሳሌ፡- ዳንኤል 11፡21-45 የሚናገረው ስለ አንጾኪየስ ኢጲፋንስ ሲሆን፥ ስለ ሐሰተኛው ክርስቶስም ይናገራል።)

መ. በአጠቃላይ ሕዝብ ጥፋት ላይ የሚያተኩሩ (አፖካሊፕቲክ) ትንቢቶች፡- እነዚህ ትንቢቶች ብዙ ተምሳሌቶችን የሚጠቀሙ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ለዚህች ምድር ያለው ዕቅድ የሚጠቃለልበትን የመጨረሻ ዘመን ሁኔታን የሚያመለክቱ ናቸው። አብዛኛዎቹን ተምሳሌቶች በትክክል መተርጐም ቀላል ስላልሆነ፥ ስለምን እንደሚናገሩ ለመረዳት ብንችልም እንኳ በተለየ መንገድ የተተረጐሙትን የሌሎች ሰዎችንም ትርጉሞች በመቻቻል ማስተናገድ ይኖርብናል።

12. አንዳንድ ጊዜ ነቢያት ትንቢትን ሲናገሩ መልእክታቸው የሚያስከትለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ አያውቁም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት በአንድ ጊዜ የሚፈጸሙ የሚመስሉ ሁለት አሳቦችን በአንድነት ይገልጹ ነበር። ይሁን እንጂ አሳቦቹ ሁለት የተለያዩ ጊዜያትን እንደሚናገሩ እናውቃለን። ለምሳሌ፡- ስለ ክርስቶስ የመጀመሪያና ዳግም ምጽአት በአንድ ጊዜ የሚናገሩ የነቢያት መልእክቶች አሉ። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህን አልተረዱም ነበር (ለምሳሌ፡- ዘካርያስ 12፡10-14፡21)።

ይህንን እውነት ለመረዳት በአንድ ከፍተኛና ትልቅ ተራራ ላይ ሆነህ በርቀት የሚታዩ ሌሎች ተራራዎችን እንደምትመለከት አድርገህ አስብ። እጅግ የተቀራረቡና በአንድነት ያሉ በሚመስሉ ሁለት ተራሮች መካከል ትልቅ ሸለቆ ሊኖር ይችላል። ነቢያት በከፍተኛና ትልቅ የጊዜ ተራራ ላይ ሆነው ይመለከቱ ነበር። በዚህ ጊዜ ልክ እንደ ሁለቱ ተራራዎች በአንድ

ጊዜ የሚፈጸሙ የሚመስሉትን ሁለት ድርጊቶችን ተመለከቱ፤ ነገር ግን እነዚህ ሁለት ድርጊቶች በ2000 ዓመታት ልዩነት የተፈጸሙ መሆናቸውን እናውቃለን።

13. በርካታ ትንቢቶች ለመረዳት ግልጽ የሚሆኑት ከተፈጸሙ በኋላ ነው። ስለ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድር መምጣት የተነገሩ ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን ዘመን ይኖሩ ለነበሩ ወይም ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ለነበሩ ሰዎች ግልጽ አልነበሩም። እነዚህ ትንቢቶች ግልጽ የሆኑት ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ነበር። አሁንም ገና ወደፊት ሊፈጸሙ ያሉ ትንቢቶች ለእኛ ግልጽ አይደሉም። ከተፈጸሙ በኋላ ግን ወደ ኋላ መለስ ብለን ልንመለከትና በግልጽ ልንረዳቸው እንችላለን። ስለዚህ ይህ ነገር ገና ወደ ፊት ሊፈጸሙ ስላሉ ትንቢቶች ያለንን አስተሳሰብ ላላ አድርገን እንድንይዘው ሊያስተምረን ይገባል። እንዴት እንደሚፈጸሙ አሳብ ሊኖረን ቢችልም እንኳ አፈጻጸማቸው እኛ ከምናስበው ፍጹም በተለየ መንገድ ሊሆን ይችላል።

13ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 9 አንብብ። ከላይ ኀተመለከትናቸው 13 መመሪያዎች በመጠቀም ይህንን ምዕራፍ አጥና። ሀ) በዚህ ክፍል ውስጥ ግልጽ ያልሆኑት ቃላት የትኞቹ ናቸው? ትርጉማቸውን ስጥ። ለ) የምዕራፉን ዋና ዋና ትምህርቶች ዘርዝር። ሕዝቡን ለማበረታታት፥ ለመገሠጽ ወይም ለመምከር የታቀደው እንዴት ነው? ሐ) የምዕራፉ ታሪካዊ ሥረ መሠረት ምንድን ነው? መ) በአሪት ዘዳግም 28-32 ከተጠቀሱ መርገሞችና በረከቶች ጋር ተመሳሳይነት አለውን? ካለው እንዴት? ሠ) ይህ ምዕራፍ ከየትኛው ዓይነት የነቢያት መልእክት ይመደባል? ረ) የተሰጡት የትንቢት ዓይነቶች የቅርብ ጊዜ ናቸው ወይስ የሩቅ ጊዜ፥ ወይስ የሁለቱም? የሩቅ ጊዜ ከሆኑ ተፈጽመዋልን? እንዴት? የተፈጸሙት በተምሳሌት ነው ወይስ በቀጥታ? ሰ) ከግል ሕይወትህ ወይም ከቤተ ክርስቲያንህ ጋር ልታዛምዳቸው የምትችለውን ትምህርቶች ከዚህ ክፍል ጥቀስ።

4ኛ ቀን ፡-

ስለ ትንቢት የሚቀርቡና በአተረጓጐሙ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የተለያዩ አመለካከቶች

ትንቢትን ማጥናት ቀላል አይደለም። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ሌሎች የሰጡትን ትርጉም ለመመርመር ረጃጅም ሰዓታትን የሚጠይቅ ነው። በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን አብዛኛዎቹን የነቢያት መልእክቶች ለመተርጐም በምሁራን ዘንድ አጠቃላይ ስምምነት ቢኖርም፥ ሆኖም ግን በአይሁድ ታሪክ ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ተፈጻሚነት ያላገኙትን ትንበያዎች ለመተርጎም ትልቅ ልዩነት ታይቶአል። ምሁራን፡- እነዚህ ትንበያዎች ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ቀደም ሲል በአይሁዳውያን ተፈጽመዋል ወይስ በቤተ ክርስቲያን ልምድ ውስጥ በመንፈሳዊ ሁኔታ ተፈጽመዋል? ወይንስ ደግሞ በቀጥታ የሚፈጸሙበትን መጪውን ጊዜ እየተጠባበቁ ናቸው? ሲሉ ይጠይቃሉ።

ያልተፈጸሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን በመረዳት ረገድ ከፍተኛ ልዩነቶችን የሚፈጥሩ ሁለት ዐበይት ጉዳዮች አሉ፡-

1. ትንቢቶቹን መረዳት የሚቻለው እንደተጻፉ በቀጥታ ነው ወይስ በተምሳሌታዊ መንገድ? አንዳንድ ምሁራን ወደፊት ስለሚመጣው ጦርነት፥ ስለተባበረው የእስራኤል መንግሥት ዳግም መመሥረት ወይም ወደፊት ስለሚሠራው ቤተ መቅደስ የሚናገሩ ትንቢቶች ሁሉ በተምሳሌታዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ይገምታሉ። እነዚህ ነገሮች መፈጸም ያለባቸው በቀጥታ ለአይሁድ ሕዝብ ሳይሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን ነው ይላሉ። እነዚህ ትንቢቶች እግዚአብሔር አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያመጣቸው የአንድነት፥ የሰላም ወይም ዘላለማዊ የሆነ አምልኮ መግለጫዎች ናቸው የሚል እምነት አላቸው።

ሌሎች ምሁራን ግን ይህ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጐም አጥጋቢ ነው ብለው አያምኑም። ቀጥተኛ የሚመስሉትን ትንቢቶች (ለምሳሌ፡- ስለ ቤተ መቅደሱ መሠራት የተነገረው ሕዝቅኤል 40-48) ተምሳሌታዊ አድርገን መውሰድ ከጀመርን ትንቢትን እንዴት እንደምንተረጉምና እንደምናዛምድ፥ እንዲሁም ልንረዳው የሚገባን በቀጥታ ይሁን በተምሳሌት የምንወስንበት መመዘኛ አይኖረንም ይላሉ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ አመጣጥ፥ በቤተ ልሔም ስለ መወለዱ፥ ወደ ግብጽ ስለ መሸሹ፥ ስለ ሞቱና ትንሣኤው የተነገሩ አብዛኛዎቹ ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን በተነገሩበት አኳኋን በቀጥታ መፈጸማቸውን ይጠቁማሉ፤

ስለዚህ አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ቀጥተኛ አይደሉም፤ የምንረዳቸውና የሚፈጸሙትም በተምሳሌታዊ ሁኔታ ነው ለማለት የምንችልበት ግልጽ መሠረታዊ ምክንያት የለንም ይላሉ። እነዚህ ምሁራን ትንቢቶችን መጀመሪያ ከተጻፉበትና መልእክቱ የተጻፈላቸው አይሁድም ከተረዱበት መንገድ ጋር በእጅጉ ተቀራራቢ በሆነ አኳኋን መተርጐምን ይመርጣሉ። ለምሳሌ፡- ሕዝቅኤል 40-48 በግልጽ የሚያስተምረው ስለ እስራኤል ሕዝብ መመለስ፥ ስለ ምድሪቱ መከፋፈል፥ ስለ ቤተ መቅደሱ መሠራትና ስለ መሥዋዕት አቀራረብ ነው። ስለዚህ ይህ ሁሉ በመጨረሻው ዘመን ልክ እንደተነገረው ይፈጸማል ብለው ያምናሉ።

2. በእግዚአብሔር የወደፊት ዕቅድ ውስጥ እስራኤል ያላት ስፍራ፡- በብሉይ ኪዳን ዘመን አይሁድ ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደነበሩ ምሁራን በሙሉ ይስማማሉ። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በዚህ ዘመን ያለች የእግዚአብሔር ሕዝብ ማኅበር እንደሆነች ያምናሉ፤ ነገር ግን እስራኤላውያን በእግዚአብሔር የወደፊት ዕቅድ ውስጥ ስላላቸው ስፍራ ምሁራን አይስማሙም። እግዚአብሔር ለአይሁድ ወደፊት ሊፈጽምላቸው ተስፋ የሰጣቸው ልዩ ዕቅድ አለውን? ወይስ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረው የልዩነት ግድግዳ ሙሉ በሙሉ ፈርሶ፥ በብሉይ ኪዳን ስለ አይሁድ የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን መፈጸም ያለባቸው ናቸው? ከእንግዲህ የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች እንጂ በሥጋ የአብርሃም ልጆች የሚባሉ የሉም ማለት ነውን? (ገላትያ 3:29፤ 4:28-31፤ ሮሜ 9:8)።

> 14ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፡- ገላትያ 3:29፤ 4:28-31፤ ሮሜ 9:8። ጥቅሶቹ ስለ እውነተኞች አይሁድና ስለ እውነተኞች የአብርሃም ልጆች ምን ይላሉ?

አንዳንድ ምሁራን እግዚአብሔር በሥጋ የአብርሃም ልጆች ከሆኑ እስራኤላውያን ጋር የነበረው ዕቅድ ያከተመ ይመስላቸዋል። አሁን የሚሠራው አይሁድና አሕዛብ ከሚገኙበት ቤተ ክርስቲያን ጋር ብቻ ነው ይላሉ። ስለዚህ እስራኤልና ይሁዳ እንደገና እንደሚዋሐዱ፥ ምድራቸውን ወደፊት እንደሚያገኙ ወይም ወደ ምድራቸው እንደሚመለሱ ወዘተ. የተነገሩት ትንቢቶች ቤተ ክርስቲያንን በሚያመለክት መንገድ በተምሳሌት መተርጐም አለባቸው ይላሉ።

15ኛ ጥያቄ. ሮሜ 11:25-32 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ለእስራኤል ነገድ የተለየ ዕቅድ እንዳለው የሚያስተምሩ ናቸው ወይስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ናቸው? መልስህን አብራራ።

ሌሎች ምሁራን እግዚአብሔር የአብርሃም የሥጋ ዝርያ ለሆኑት አይሁድ አሁንም ቢሆን ዓላማ አለው ይላሉ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ከነዓን ምድር፥ ከኢየሩሳሌም የዳዊት ልጅ እንደሚገዛቸው፥ ወዘተ. ልዩ በሆነ መንገድ የሰጣቸው የተስፋ ቃል ወደፊት በቀጥታ ይፈጸማል። ስለዚህ እነዚህ ምሁራን ያልተፈጸሙ ትንቢቶች የሚፈጸሙት በተምሳሌት ለቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፥ በቀጥታ ለእስራኤል ሕዝብ እንደሆነ ይናገራሉ።

ስለ እነዚህ ጉዳዮች ያለን ቅድመ አስተሳሰብ እነዚህን ያልተፈጸሙ ትንቢቶች በምንተረጉምበት ሂደት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ልብ ልንል ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች በትንቢት መጻሕፍት አተረጓጎም ረገድ በከፍተኛ ደረጃ የሚለያዩት በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ ባላቸው የተለያየ ግንዛቤ ነው። ይህ ነገር ከርስቲያኖች በመሆናችን ወይም ባለመሆናችን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር አለመሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በሁለቱም አመለካከቶች ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረው ነገር እነርሱ እንደሚያስቡት ብቻ እንደሆነ የሚያምኑ ጠንካራ የክርስቲያን ምሁራን አሉ። ሆኖም ስለ ሁለቱ አመለካከቶች ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ማግኘት አስፈላጊ ነው። የትኛው አመለካከት የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሚመስልና ያንንም ያልነው ለምን እንደሆነ ለራሳችን መወሰን አለብን። ነገር ግን እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት ከእኛ የተለየ ግንዛቤና አተረጓጎም ካላቸው ጋር በመቻቻል ለመኖር መዘጋጀት አለብን።

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የሚቻል ከሆነ፥ ከተለያዩ የክርስትና እምነት ክፍሎች ከሆኑና በሚገባ ከተማሩ ሰዎች ጋር በመነጋገር ስለ መጪው ጊዜ ምን እንደሚያስቡ ተረዳ። የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች እንዴት መተርጎም እንዳለባቸውና እግዚአብሔር ለእስራኤል ስለወጠነው የወደፊት ዕቅድ ያላቸው አስተሳሰብ ምንድን ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ስለ እነዚህ

ሁለት ጉዳዮች ያላት እምነት ምንድን ነው? ለምን? የቤተ ክርስቲያንህን መጋቢ ወይም ወንጌላዊን ጠይቅ።


ምሁራን አብዛኛዎቹን ያልተፈጸሙ ትንቢቶች በመተርጐም ረገድ ይረዳቸው ዘንድ እያንዳንዱን ትንቢት ለመረዳት የሚጠቅም ሰፋ ያለ መሠረት ጥለዋል። በአጠቃላይ ሰዎች ትንቢቶችን ለመተርጐም የሚጠቀሙባቸው መሠረቶች ሦስት ዓይነት ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት አመለካከቶች ትንቢቶችን በተምሳሌታዊ ሁኔታ የሚተረጕሙበት ሁኔታዎች ናቸው። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንንና እስራኤልን እንደ አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ አድርገው የሚቈጥሩና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንና ለእስራኤል አንድ እንጂ የተለያየ ዕቅድ የለውም የሚሉ ናቸው።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለሰው ከአንድ ሺህ ዓመት በኋላ ነው የሚለው አመለካከት (ድኅረ ሺህ ዓመት ወይም ፖስት-ሚሌኒያሊዝም)፡- ይህም አመለካከት እግዚአብሔር አንድ ሕዝብ ብቻ እንዳለው ያምናል። ያም ሕዝብ በብሉይ ኪዳን እስራኤል የተባለው ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በመባል ይጠራል። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል የገባው ቃል ኪዳን የተፈጸመው በቀጥታ ለእስራኤል ሳይሆን፥ በመንፈሳዊ መንገድ ለቤተ ክርስቲያን ነው። ወንጌል በዓለም ሁሉ ስለሚሰፋፋ ዓለም በሙሉ በክርስትና እምነት ትለወጣለች። ክርስቶስ መጀመሪያ ሲመጣ የተጀመረው የእግዚአብሔር መንግሥት ዓለምን ሁሉ እስኪያጠቃልል ድረስ ይሰፋፋል። ከዚያም ለረጅም ጊዜ በምድር ላይ ሰላም ከሰፈነ በኋላ ክርስቶስ ይመጣል። ሰው ሁሉ ከተነሣና ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ዘላለማዊ ወደሆነው መንግሥተ ሰማያት ወይም ገሃነም ይገባል። ኢየሱስ አንድ ሺህ ዓመት እንደሚነግሥ የተነገረው ቃል ተምሳሌታዊ ሲሆን፥ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገበት ጊዜ ጀምሮ ለዘላለም ሊነግሥ እስከሚመለስበት ድረስ ያለው ወቅት ነው። ከአንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ይህ አመለካከት የታወቀ ነበር። ብዙ ክርስቲያኖች ክርስትና በፍጥነት በማደግ ዓለምን ሁሉ ያጠቃልላል ብለው ያስቡ ነበር፤ ከጦርነቶቹ በኋላ ግን ይህ አመለካከት እስከዚህም የታወቀ አልነበረም።

ማስታወሻ፡- ሚሌኒየም የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ማለት ነው (ራእይ 20፡1-6)።


17ኛ ጥያቄ. ሀ) ማቴዎስ 24፡14 ተመልከት። ወንጌል በዓለም ሁሉ ሊዳረስ የሚችልባቸው አንዳንድ መንገዶች አሉን? ለ) አብዛኛው ሕዝብ ክርስቲያን የሚሆንበት ጊዜ የሚመጣ ይመስልሃል?

ቀጥሎ ከላይ የተመለከትነውን አመለካከት የሚያንጸባርቅ ሥዕላዊ መግለጫ እናያለን። ወደ ጎን የተሠመረው መሥመር የጊዜን ወይም የታሪክን ሂደት የሚያሳይ ነው። ከፍጥረት ጀምሮ የጊዜ ፅንሰ አሳብ እስከሚያበቃበት እስከ ዘላለም ድረስ ይሄዳል?





2. በምድር ላይ የአንድ ሺህ ዓመት መንግሥት የሚባል ነገር የለም የሚለው አመለካከት (አሚሌኒያሊዝም)፡- እነዚህ ክርስቲያኖች እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ መልካምና ክፉ በምድር ላይ ይኖራሉ ይላሉ። ክርስቶስ በአካል በምድር ላይ የሚነግሥበት ጊዜ ከቶ አይኖርም። የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ጉዳይ ተምሳሌታዊ ነው። ክርስቶስ በአሁኑ ጊዜ በመንፈሱ በሕዝቡ ልብ ውስጥ ነግሦአል፤ ከሞቱና በሰማይ ከእርሱ ጋር ካሉ ቅዱሳን ጋር ነግሦአል። በመጨረሻው ዘመን በምድር ላይ ሁኔታዎች ሁሉ ይከፋሉ። ክሕደት ይጨምራል። ከዚያም ክርስቶስ በክብሩ ይመጣና ጠላቶቹን ሁሉ ያሸንፋቸዋል። የሞቱት ይነሡና ይፈረድባቸዋል። ከዚያም በኋላ ሰው ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት ወይም በገሃነም ውስጥ ለዘላለም ይገባል። እስራኤልና ቤተ ክርስቲያን አንድ ስለሆኑ በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል የተሰጡት ተስፋዎች ሁሉ በመንፈሳዊ ረገድ ለቤተ ክርስቲያን

ይፈጸማሉ። ይህ እስካሁን ድረስ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው።




3. ክርስቶስ ከሺሁ ዓመት መግሥት በፊት ይመጣና በምድር ላይ ለአንድ ሺህ ዓመት ይነግሣል የሚለው አመለካከት (ቅድመ ሺህ ዓመት ፕሪሚሌኒያሊዝም)፡- ይህ አመለካከት እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን በቀጥታ ለመውሰድ የሚፈልግ ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። ቃል ኪዳኑም ለእነርሱ ሊፈጽምላቸው የሚገባ ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያለው ዕቅድ ለቤተ ክርስቲያን ካለው ዕቅድ የተለየ ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች በዚህ ዘመን መጨረሻ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን እንደሚመጣ ያምናሉ። ከዚያም ክርስቲያኖች ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ ከእርሱ ጋር ይኖራሉ። በምድር ላይ ግን ታላቅ የመከራ ጊዜ ይጀምራል። የእግዚአብሔር ቍጣም በሰዎች ሁሉ ላይ ይፈሰሳል። ቀጥሎ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ተመልሶ የክፋት ኃይላትን በማሸነፍ በምድር ላይ ለአንድ ሺህ ዓመት ይነግሣል። ይህ ዘመን ታላቅ ሰላምና ብልጥግና የሰፈነበት ይሆናል። የአዳም መርገም ከፍጥረት ሁሉ ላይ ይወገዳል። ክፋት እንዳይሠለጥን በክርስቶስ ይታገዳል። በዚህ አንድ ሺህ ዓመት እስራኤል ከፍ ያለ ድርሻ ታበረክታለች። ምሁራን እንግዲህ በዚህ ጉዳይ ላይ ነው እጅግ የተለያየ አሳብ ያላቸው። ሆኖም ግን ከእስራኤል ሕዝብ አብዛኛው ያምንና በተስፋይቱ ምድር ይሰበሰባል፤ እስራኤልና አሕዛብም ይፈረድባቸዋል። በዚህ ጊዜ ለእስራኤል የተሰጡ የተስፋ ቃሎች በአንድ መንገድ ይፈጸማሉ። ከሺህ ዓመት በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የሚካሄድ ጦርነት አለ። ክርስቶስ የክፋትን ኃይላት ሁሉ ያሸንፋል። ባልዳኑት ሰዎች ላይ የመጨረሻ ፍርድ ይሰጣል፤

እነርሱም ወደ ገሃነም ይገባሉ። ከዚያም አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይፈጠርና ዘላለማዊነት ይጀመራል።




በሦስተኛው አመለካከት ውስጥ ሦስት መጠነኛ ልዩነቶች አሉ። አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖች ከታላቁ መከራ በፊት ይነጠቃሉ ይላሉ። ሌሎች ክርስቲያኖች መነጠቅ የሚሆነው በመከራው ዘመን መካከል ነው ሲሉ፥ የቀሩት ደግሞ ክርስቲያኖች በታላቁ የመከራ ዘመን ውስጥ ካለፉ በኋላ ይነጠቁና በምድር ላይ ለመግዛት ወዲያውኑ ከክርስቶስ ጋር ይመለሳሉ ብለው ያምናሉ።

የአተረጓጎም ችግር የሌለበት አመለካከት የለም። ለዚህ የጥናት መጽሐፍ አዘጋጅ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ ስለ ሺህ ዓመቱ መንግሥት የሚያስተምረው የመጨረሻው አመለካከት ይበልጥ ግልጽ ሆኖ ይታየዋል።

ከእነዚህ ሦስት አመለካከቶች የምንቀበለው የትኛውም ይሁን ብዙዎቹን ትንቢቶች የምንረዳበትን መንገድ ይወስናል። በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ እስካሁን ወዳልተፈጸሙ ትንቢቶች ላይ በምንደርስበት ጊዜ፥ ተርጓሚው እነዚያን ትንቢቶች አስቀድሞ ከወሰነው አመለካከት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ይሞክራል።

18ኛ ጥያቄ፥ እነዚህን ሦስት አመለካከቶች አጥና። ሀ) የምትቀበለው የትኛውን አመለካከት ነው? ለምን?

ለ) ሌሎች ክርስቲያኖች ይቀበሉታል የምትለው የትኛውን አመለካከት ነው? ሐ) የእነርሱ አመለካከት ከአንተው የሚለየው እንዴት ነው? መ) የትንቢት አመለካከቶችን በሚመለከት ስለ እነዚህ ልዩነቶች መከራከር የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

**5ኛ ቀን፡-**

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

**ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ**

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት

ሀ. 1) በብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢይ ምን ነበር? 2) ይህ ግንዛቤ ብዙ ሰዎች ዛሬ ስለ ነቢያት ማንነት ካላቸው አስተሳሰብ የሚለየው እንዴት ነው? 3) «ነቢይ» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት። ስለ አዲስ ኪዳን ነቢያት የተጠቀሱትን የተለያዩ ነገሮች ዘርዝር። 4) ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ነቢያት አሉን? መልስህን አብራራ። 5) ነቢያት ካሉ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የሚመሳሰሉት ወይም የሚለያዩት እንዴት ነው? 6) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ድርሻ ምንድን ነው? 7) እውነተኞች ነቢያትን ከሐሰተኞች እንዴት መለየት እንችላለን?

ለ. እያንዳንዱ ምሁር ስለ ኢሳይያስ 9 ያደረገውን ጥናት አወዳድር። 1) እያንዳንዱ ተማሪ ይህንን ጥያቄ የመለሰው እንዴት ነው? 2) በመልስ አሰጣጥ ረገድ ከቀረቡት መመሪያዎች የትኞቹን ተጠቅመዋል? 3) በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከሕይወትህ ጋር የምታዛምዳቸው ትምህርቶች ምንድን ናቸው?

ሐ. ትንቢትን ስለሚመለከቱት ሦስት የተለያዩ አመለካከቶች ተወያዩበት። 1) እነዚህ አመለካከቶች የሚመሳሰሉትና የሚለያዩት

እንዴት ነው? 2) የአንተ አመለካከት የትኛው ነው? ለምን? 3) ይህንን በሚመለከት ከአንተ የተለየ አመለካከት ያላቸው የአንዳንድ ክርስቲያኖች አመለካከቶች ምንድን ናቸው? የተለየ አመለካከት ያላቸው ለምንድን ነው? 4) ከትንቢቶቹ ይልቅ ላንስማማባቸው የምንችል ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የትኞቹ ናቸው?

5. ጸሎት

# ትምህርት ስምንት

## 1ኛ ቀን፡- የትንቢተ ኢሳይያስ መግቢያ

**1ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪ ነው፡- እርሱም በሕዝብ መሪዎች ላይ፥ ወደ ክርስቲያን ሕይወት በሚመጣ በረከት ላይ፥ በምድር በሚመጡ ፍርዶች ላይ፥ በምድር በሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ነው። አንድ ክርስቲያን ይህን እውነት ከተረዳ በክርስትና ሕይወቱ የሚያበረታታው እንዴት ነው?**

በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ ታላላቅ የትንቢት መጻሕፍት አንዱ ትንቢተ ኢሳይያስ ነው። ታላቅ የተባለባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ በመጀመሪያ፥ ትንቢተ ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ግርማ፥ ቅድስናና በነገሮች ሁሉ ላይ ስላለው ሉዓላዊ ሥልጣን ግልጽ የሆነ ትምህርት ይሰጣል። ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ የማያሻማ ገለጻ ያቀርባል። አንድ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የበለጠ በተረዳ ቍጥር፥ በሕይወቱ በሚገጥሙት አስቸጋሪና አጠራጣሪ ጉዳዮች ውስጥ በእግዚአብሔር በመተማመን በእርግጠኝነት መጓዙን ይቀጥላል። ሁለተኛ፥ ትንቢተ ኢሳይያስ ከመዝሙረ ዳዊት በቀር ከማንኛቸውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ይልቅ በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶአል፤ ይህም 80 ጊዜ ያህል ነው። በሦስተኛ ደረጃ፥ ትንቢተ ኢሳይያስን ታላቅ ያሰኘው በርካታ የወንጌል መመሪያዎችን መያዙ ነው። በመሠረቱ አንዳንዶች ትንቢተ ኢሳይያስን «አምስተኛው ወንጌል» በማለት ይጠሩታል። ይህም የሆነው፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ክርስቶስን የሚያሳዩ ብዙ ተምሳሌቶች ስላሉና ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሚሆንበት መንገድ በግልጽ ስለቀረበ ነው (ለምሳሌ፡- 1፡18፤ 44፡22፥ 55፤ 64፡6)።

**2ኛ ጥያቄ፥ በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የሚገኙ ከዚህ ቀደም ያበረታቱህ አንዳንድ ክፍሎችን ጥቀስ።**

ትንቢተ ኢሳይያስ ከታላላቅ የነቢያት መጻሕፍት መካከል የመጀመሪያው ነው። ካለፈው ሳምንት ትምህርት እንደምታስታውሰው፥ ከትንቢተ ኢሳይያስ ጀምሮ እስከ ኤርምያስ ድረስ ያሉት መጻሕፍት

ከታላላቅ ነቢያት ክፍል የሚመደቡ ናቸው። የታላላቅ ነቢያት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ፈቃድና ወደ ፊት ስለሚፈጸሙ ነገሮች የነበረንን እውቀት የሚያጐለብቱ ናቸው። የሚከተለውን የታላላቅ ነቢያት ሰንጠረዥ አጥና፡-

| የነቢዩ ስም | የተጻፈበት ጊዜ | ለማን እንደተጻፈ | የአይሁድ መሪ | የአሕዛብ መንግሥት |
|---|---|---|---|---|
| ኢሳይያስ | 740-680 ዓ.ዓ. | ለይሁዳ | ዖዝያን-ሕዝቅያስ | አሦር |
| ኤርምያስ (ሰቆቃወ ኤርምያስ) | 627-580 ዓ.ዓ. | ለይሁዳ | ኢዮስያስ-ሴዴቅያስ | አሦር |
| ሕዝቅኤል | 593-573 ዓ.ዓ. | በምርኮ ለነበሩ | | ባቢሎን |
| ዳንኤል | 605-539 ዓ.ዓ. | በምርኮ ለነበሩ | | ባቢሎን |

ትንቢተ ኢሳይያስ በይሁዳ ምድር ባሉት በአይሁድ ሕዝብ ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ጥፋት አስቀድሞ ተንብዮ ነበር፤ ዳሩ ግን የመጽሐፉ የመጨረሻ ግማሽ ክፍል፥ በምርኮ የተወሰደው ሕዝብ የሚለቀቅበትንና አይሁድ ወደ ምድራቸው የሚመለሱበትን ጊዜ ያመለክታል። ኢሳይያስ እግዚአብሔር በሕዝቦች ሁሉ ላይ ያለውን ሉዓላዊ ሥልጣን በማመልከት በምርኮ ይኖሩ የነበሩት ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት እንዳይተው ለማጽናናትና ለመምከር ፈልጎ ነበር።

## የትንቢተ ኢሳይያስ ጸሐፊ

ትንቢተ ኢሳይያስ ስያሜውን ያገኘው መጽሐፉን ከጻፈው ነቢይ ስም ነው። በኢሳይያስ 1፡1 እንደተገለጸው፥ መጽሐፉ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ የተቀበለው ራእይ ነው።

ሰዎች ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ የትንቢተ ኢሳይያስ ጸሐፊ ኢሳይያስ ራሱ እንደሆነ ያምኑ ነበር። የመጽሐፉ የመጀመሪያ ቊጥር የሚናገረው ይህንኑ ስለሆነ የምንጠራጠርበት አንዳችም ምክንያት የለም። ሆኖም ባለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ፥ ምሁራን ሙሉ መጽሐፉን የጻፈው ኢሳይያስ ስለ መሆኑ ጥያቄ ማንሣት ጀምረዋል። የመጽሐፉን የመጀመሪያ ግማሽ ክፍል (ከምዕራፍ 1-39) ከመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል (ከምዕራፍ 40-66) ጋር ሲያወዳድሩ በርካታ ልዩነቶችን አዩ። ከዚህ የተነሣ፥

ትንቢተ ኢሳይያስን የጻፈው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጡ የተለያዩ ፅንሰ አሳቦች ተፈጠሩ።

1. የትንቢተ ኢሳያይስ ጸሐፊዎች ሁለት ናቸው፤ የመጀመሪያው፥ ኢሳይያስ በመባል የሚታወቅና የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፍሎ በቆየባቸው ዘመናት የኖረ ሲሆን፥ የጻፈውም ከምዕራፍ 1-32 ያለውን ክፍል ነው። ሁለተኛው ጸሐፊ ግን አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ ከተመለሱ በኋላ የኖረና ከምዕራፍ 33-66 ያለውን ክፍል የጻፈ ሰው ነው። (አንዳንዶች የመጀመሪያው ጸሐፊ ከምዕራፍ 1-39 ያለውን፥ ሁለተኛው ጸሐፊ ደግሞ ከምዕራፍ 40-66 ያለውን ክፍል ጽፏል ይላሉ)። ዛሬ ብዙ ምሁራን፥ በተለይም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት መጽሐፍ መሆኑን የማያምኑ ሰዎች የሚቀበሉት ይህን አመለካከት ነው።

2. ትንቢተ ኢሳይያስን የጻፉት ሦስት ሰዎች ናቸው። የመጀመሪያው ጸሐፊ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፍሎ በቆየበት ዘመን የኖረ ሲሆን፥ ከኢሳይያስ 1-39 ያለውን ክፍል ጽፏል። ከ580 ዓ.ዓ. በኋላ፥ ሁለተኛው ጸሐፊ ከኢሳይያስ 40-55 ያለውን ክፍል የጻፈ ሲሆን፥ በ444 ዓ.ዓ. በነህምያ ዘመን አካባቢ ይኖር የነበረ ሌላ ሦስተኛ ጸሐፊ ከኢሳይያስ 56-66 ያለውን ጽፏል።

3. ትንቢተ ኢሳይያስን በሙሉ የጻፈው ኢሳይያስ ነው። አይሁድና ክስርቲያኖች በዘመናት ሁሉ ውስጥ የያዙት አቋም ይህ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት መጽሐፍ መሆኑን በሚያምኑ ክርስቲያኖች ዘንድ አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያለው አቋም ይህ ነው።

በምሁራን መካከል ይህ ልዩነት የሚታየው ለምንድን ነው? ቢያንስ ሁለት ጸሐፊዎች ነበሩ የሚል አቋም ያላቸው ጸሐፊዎች የሚያቀርቡት ምክንያት እንደሚከተለው ነው፦

ሀ. በርካታ ምሁራን ትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የምንመለከተው ዓይነት ዝርዝርና ስሕተት የሌለበት ትንበያ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የተመለከተ አንድ ሰው ካልጻፈው በስተቀር ሌላ ሊሆን አይችልም ብለው ያምናሉ። በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የምንመለከታቸው አብዛኛዎቹ ትንቢቶች ግልጽና ጥርት ያሉ ሆነው ያለ አንዳች

ስሕተት የተፈጸሙ ስለሆኑ፥ መጽሐፉ የተጻፈው ድርጊቶቹ ከተፈጸሙ በኋላ ነው ይላሉ። ለምሳሌ፦ ከ740-700 ዓ.ዓ. የኖረው ኢሳይያስ እስራኤላውያንን ከባቢሎን ምርኮ ነፃ የሚያወጣው የአሕዛብ ንጉሥ ቂሮስ ተብሎ እንደሚጠራ ተንብዮ ነበር (ኢሳይያስ 44፡28፤ 45፡1)። እንደምታውቀው፥ ይህ ትንቢት የተፈጸመው የፋርስ ንጉሥ የሆነው ቂሮስ ከ200 ዓመታት በኋላ የባቢሎንን መንግሥት በማሸነፉ እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው እንዲመለሱ በፈቀደ ጊዜ ነበር።

ለ. እነዚህ ምሁራን በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የሚገኙ ትንቢቶች በሌሎች መጻሕፍት ከሚገኙ ትንቢቶች ሁሉ የተለዩ ናቸው ይላሉ። ሊመጣ ስላለው ምርኮ ሰፊና ግልጽ ያልሆኑ ጥቅሶች ከመሆን ይልቅ፥ ትንቢቶች እጅግ ዝርዝር ወደሆነ ነገር በመግባት ነፃ የመውጣቱን ጉዳይ የሚያስፈጽመውን ሰው ስም እስከ መጥቀስ ድረስ እንኳ ዘልቀዋል።

ሐ. እነዚህ ምሁራን፥ የመጽሐፉን የመጀመሪያ ግማሽ ከሁለተኛው ግማሽ ክፍል ጋር በምናወዳድርበት ጊዜ የቋንቋ አጠቃቀማቸው ፍጹም የተለያየ ስለሆነ የተጻፉት በሁለት የተለያዩ ሰዎች መሆን አለበት ይላሉ። የትንቢተ ኢሳይያስ የመጀመሪያ ግማሽ ክፍል ስለ ፍርድና ጥፋት የሚናገር ሲሆን፥ በሰቆቃ ትንበያዎች የተሞላ ነው። ሁለተኛው ግማሽ ክፍል ግን በይበልጥ ሥነ- ግጥማዊና ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት የያዘ ነው። የሚያተኩረው በማበረታቻ መልእክት ላይ ሲሆን፥ የተጻፈውም ሕዝቡ በምርኮ ውስጥ እንዳለ እንጂ ምርኮው ገና ከ150 ዓመታት በኋላ እንደሚፈጸም ተደርጎ አይደለም። የትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ የመጀመሪያ ግማሽ የሚያተኩረው በነገሥታትና እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ከሚያመጣው ፍርድ በኋላ በሚኖሩ ቅሬታዎች ላይ ሲሆን፥ ሁለተኛው ግማሽ ክፍል ግን ሊመጣ ባለው የእግዚአብሔር አገልጋይና እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚያመጣው ደኅንነት ላይ ነው።

መ. ለነቢያትና ለትንቢታቸው ህልውና ዐበይት ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ፥ በዘመናቸው ለነበሩ ሰዎች አስፈላጊ የሆነ መልእክት

መስጠት እንደነበረ ተመልክተናል። የትንቢተ ኢሳይያስ የመጨረሻ ግማሽ ክፍል ግን በነቢዩ ዘመን በጊዜው የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት አይመስልም። ይልቁንም የይሁዳ ሕዝብ በምርኮ እንዳሉ አድርጎ የሚናገር ይመስላል። ስለዚህ ይህ ትንቢት የተሰጠው እስራኤል በምርኮ እንዳለች እንጂ በምርኮ ከመወሰዳቸው ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት እንዳልሆነ የሚያመለክት ይመስላል።

**3ኛ ጥያቄ፥ አንድ ሰው ስለ ትንቢትና እግዚአብሔር የወደፊቱን ጉዳይ አስቀድሞ ለማመልከት ስላለው ችሎታ የሚኖረው አመለካከት በአቋም ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር፥ እነዚህ አመለካከቶች እንዴት ያሳዩናል?**

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በአንድ ጸሐፊ ብቻ ነበር የሚል አመለካከት ያላቸው ሰዎች ይህን አመለካከት የሚቀበሉት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፦

1. የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ትንቢቱ እንዴት እንደተፈጸመ ለማሳየት ከትንቢተ ኢሳይያስ የጠቀሱት ከመጀመሪያውም ከሁለተኛውም ግማሽ ሲሆን፥ ሁለቱንም ክፍል የጻፈው ኢሳይያስ እንደሆነ ተናግረዋል (ለምሳሌ፦ ማቴዎስ 3፡3፤ 12፡17-21፤ ሉቃስ 3፡4-6፤ ዮሐንስ 12፡38-41፤ የሐዋርያት ሥራ 8፡28-33)። አዲስ ኪዳንን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፉት ሰዎች ትንቢተ ኢሳይያስን በሙሉ የጻፈው ኢሳይያስ ነው ብለው እንደነበር ግልጽ ነው።

2. ከትንቢተ ኢሳይያስ ዐበይት መልእክቶች አንዱ፥ እግዚአብሔር የመጪውን ጊዜ ሁኔታ በመተንበይ በዘመናት ውስጥ የተለያዩ ድርጊቶች ይፈጸሙ ዘንድ ታሪክን ሁሉ የሚመራ መሆኑ ነው (ኢሳይያስ 42፡9፤ 46፡8-10)። ስለዚህ ክርስቲያኖች መጪውን ጊዜ በሚመለከት ስለተነገሩትና በትክክል ስለተፈጸሙት ትንቢቶች መደነቅ አይኖርባቸውም።

3. አንድ ሰው፥ በእግዚአብሔር የወደፊት ሁኔታዎችን መቆጣጠር ችሎታ የሚያምን ከሆነ፥ እንዲሁም ምንም ያህል የዓመታት ገደብ ይኑር፥ እግዚአብሔር የሚፈጸመውን ነገር ከመሆኑ አስቀድሞ የሚያውቅና መልእክቱን ለቀድሞዎቹ ነቢያት መስጠቱን የሚቀበል

ከሆነ፥ እግዚአብሔር የቂሮስን ስም የመሳሰሉትን ግልጽ ትንቢቶች ለመስጠት እንደሚችል የሚጠራጠርበት ምክንያት የለም። እግዚአብሔር በዚህ መልክ ሊሠራ እንደሚችል እስካመንን ድረስ፥ ሌሎች ጸሐፊዎችን የምንፈልግበት ምክንያት የለም።

4. የመጽሐፉ የመጀመሪያና ሁለተኛ ግማሽ ክፍል ቋንቋው በእጅጉ የተለያየው፥ የባቢሎን ምርኮ የማይቀር መሆኑን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለኢሳይያስ ከገለጸለት በኋላ፥ ምርኮው ገና ያልተፈጸመ ቢሆንም እንኳ የማበረታቻ ቃላት እንዲጽፍ ስለመራው ነው። የመጽሐፉ የመጀመሪያና ሁለተኛ ክፍል ዓላማዎች ፍጹም የተለያዩ ናቸው። የመጽሐፉ የመጀመሪያ ግማሽ፥ እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌምና የይሁዳን ከተሞች መደምሰስ አስቀድሞ የተናገረበትና ይህ ጥፋት የሚሆነው በምን ምክንያት እንደሆነ የገለጠበት ክፍል ነው። እነዚህ ድርጊቶች መፈጸማቸው የማይቀርና እርግጠኞች ስለነበሩ ኢሳይያስ ገና ከ150 ዓመታት በኋላ የሚፈጸመውን ነገር ልክ እንደተፈጸመ በመቁጠር ይናገራል። በመጽሐፉ ሁለተኛ ግማሽ ክፍል ደግሞ ኢሳይያስ ምርኮው የማይቀር መሆኑን በግልጽ የሚፈጸመው ገና ከ150 ዓመታት በኋላ ቢሆንም እንኳ አይሁድ ልክ በምርኮው ውስጥ እንዳሉ አድርጎ ይናገራል። ይህ የተጻፈው እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ባለሥልጣን እንደሆነና ታሪክን ወደሚጠቃለልበት ወደ መጨረሻው ዘላለማዊ መንግሥት እንደሚመራ በማሳየት አይሁድን ለማበረታታት ነበር።

5. በትንቢተ ኢሳይያስ የመጀመሪያና ሁለተኛ ግማሽ ክፍል መካከል ተመሳሳይነት ያላቸው በርካታ ነገሮች ይገኛሉ። በትንቢተ ኢሳይያስ የመጀመሪያ ግማሽ ክፍል ውስጥ ሳይቀር፥ ኢሳይያስ ሊመጣ ስላለው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት የገለጠበትን የማበረታቻ ቃላት እናገኛለን፤ (ለምሳሌ፦ ኢሳይያስ 2፡1-5)። በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ለመጥራት የተጠቀመበት «የእስራኤል ቅዱስ» የሚለው ልዩ ስም ይገኛል፤ (ለምሳሌ፦ ኢሳይያስ 1፡2፤ 1፡5-6፤ 5፡27፤ 52፡13፤ 53፡4-5፤ 57፡15 ወዘተ.)።

ስለዚህ የትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፍ የጻፉት ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ሰዎች ናቸው ብለን የምናምንበት አንዳችም ምክንያት የለም። ትንቢተ ኢሳይያስን በሙሉ የጻፈው ኢሳይያስ እንደሆነና እግዚአብሔር አንዳንድ አስደናቂ የሆኑ ትንቢቶችን እንዲጽፍ እንዳደረገው ማመን ለእኛ ከሁሉም የተሻለ ነገር ነው።

4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር የወደፊቱን ነገር ማወቅና ይህንንም በዝርዝር መግለጥ አስቸጋሪ ያልሆነው ለምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔር መጪውን ጊዜ እንደሚቆጣጠር አጥብቆ ማመን፥ ትንቢተ ኢሳይያስን ለመጻፍ እግዚአብሔር ይህን ነቢይ እንደመራው ለማመን እንዴት ይረዳናል? ሐ) ምን እንደሚሆን በማናውቀው በራሳችንና በአገራችን የወደፊት ሁኔታ ላይ ታምነን እንድንኖር ይህ አመለካከት የሚረዳን እንዴት ነው?

## የኢሳይያስ ሥረ- መሠረት

1. ኢሳይያስ የኖረበት ዘመን ታሪካዊ ሥረ- መሠረት፡-

5ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 1፡1 እና 2ኛ ነገሥት 15-20 አንብብ። ሀ) ኢሳይያስ ባገለገለባቸው ዘመናት የነበሩትን ነገሥታት ስም ዘርዝር።
ለ) የእነዚህ ነገሥታት ባሕርይ ምን ይመስል ነበር?
ሐ) በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በእስራኤልና በይሁዳ የተከናወኑ ዋና ዋና ድርጊቶች ምን ነበሩ?

ነቢዩ ኢሳይያስ የኖረውና የሠራው ለብዙ ዓመታት ነበር። መቼ እንደተወለደ ባናውቅም እንኳ የነቢይነት አገልግሎቱን የጀመረው ንጉሥ ዖዝያን በሞተበት በ740 ዓ.ዓ. ይመስላል፤ የኖረውም እስከ 680 ዓ.ዓ. አካባቢ ይመስላል። ይህ ማለት በነቢይነት ያገለገለው ከ55 ዓመታት በላይ ነበረ ማለት ነው። ኢሳይያስ በዚህ ረጅም ዕድሜው በሕዝቡ መካከል የተካሄዱ የበርካታ ለውጦች ምስክር ነበር። ሕዝቡ በከፍተኛ ደረጃ እግዚአብሔርን የወደዱበትና ደግሞም በግልጽ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁበትን ጊዜ ተመልክቷል። በሕዝብ መካከል ከፍተኛ ጥፋትና ደግሞም ከፍተኛ ብልጽግናና ሰላም የነበረበትን ወቅት ተመልክቷል።

1. *ዖዝያን*፡- የዖዝያን ዘመነ መንግሥት የይሁዳ ሕዝብ ከዳዊትና ከሰሎሞን በኋላ ደርሶበት ወደማያውቀው ከፍተኛ ሥልጣን የደረሰበት ጊዜ ነበር። የግብፅና የአሦር መንግሥታት ደካሞች ስለነበሩ ይሁዳና እስራኤል ከውጭ መንግሥታት ተጽዕኖ ነፃ የሆኑበት ጊዜ ነበር። በሰሜን በኩል የእስራኤል መንግሥት በዳግማዊ ኢዮርብዓም አመራር ተከናውኖለት፥ ከይሁዳም ጋር በሰላም የሚኖርበት ጊዜ ነበር። በይሁዳ ሕዝብ መካከል ደግሞ መንፈሳዊ መነቃቃት የነበረበት ወቅት ነበር። ዖዝያን እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ ስለነበረ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያበረታታ ነበር። ሕዝቡ ይህን ቢያደርጉም እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ጎብረት ጥልቀት እንዳልነበረው ኢሳይያስ ያውቅ ነበር። ኢሳይያስ እርሱና ሕዝቡ በቅዱሱ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን እንዳልነበሩ ባየው ራእይ ተገንዝቦአል። በዖዝያን ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ነገሮች መለወጥ ጀመሩ። ዳግማዊ ኢዮርብዓም በ753 ዓ.ዓ. ሲሞት፥ በእስራኤል ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ሽኩቻ ይካሄድ ነበር። እስራኤል በ722 ዓ.ዓ. ፈጽማ እስክትጠፋ ድረስ ሥልጣኗ ፈጥኖ እያሽቆለቆለ መሄድ ጀመረ። ዖዝያን በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ በለምጽ ስለተመታ በ750 ዓ.ዓ. ዙፋኑን ለልጁ ለኢዮአታም ማስረከቡ ነበረበት።

ኢሳይያስ ያደገው በዖዝያን ዘመነ- መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ነበር። በ740 ዓ.ዓ. የሞተውን የታላቁን ንጉሥ የዖዝያንን ሞት ሲመለከር ምናልባት ኢሳይያስ ወጣት ሳይሆን አይቀርም፤ ለነቢይነትም የተጠራው ዖዝያን በሞተበት ዓመት ነበር (ኢሳይያስ 6፡ 1)።

2. *ኢዮአታም*፡- የዖዝያን ልጅ የሆነው ኢዮአታም አብዛኛውን ዘመነ መንግሥቱን ያሳለፈው ከአባቱ ከዖዝያን ጋር ሲሆን፥ በኋለኛው ዘመኑ ደግሞ ከልጁ ከአካዝ ጋር ነበር። በመሠረቱ ኢዮአታም የአባቱን የዖዝያንን መንገድ ቢከተልም፥ በዘመነ መግሥቱ መጨረሻ ገደማ ችግር ተጀመረ። በአሦር ሣልሳዊ ቴልጌልቴልፌሶር የተባለ ንጉሥ በ745 ዓ.ዓ. ሥልጣን ያዘ፤ መንግሥቱንም ወደ ምዕራብ ማስፋፋት ጀመረ። እስራኤልንና ይሁዳን በማጥቃት አሸነፋቸውና ነገሥታቱን አስገበረ። የኢዮአታም ልጅ አካዝ በአቋሙ አሦራውያንን ይደግፍ

ስለነበር ልጁ አካዝ አብሮት ይነግሥ ዘንድ ሕዝቡ ኢዮአታምን ግድ አሉት።

3. አካዝ፡- አካዝ በሥልጣን ላይ የነበረው ከ736-735 ዓ.ዓ. ነበር፤ እግዚአብሔርን አይፈራም ነበር፤ ይልቁንም የይሁዳን ሕዝብ ወደ ከፍተኛ ክፋት መራ። አካዝ ሥልጣን ላይ በተቈናጠጠ ጊዜ፥ ሕዝቡ ለአሦር መንግሥት ይገብር ነበር፤ ዳሩ ግን እስራኤልና ሶርያ በአሦር ላይ ለማመፅ ወስነው ነበር። በዚህ ዓመፅ የይሁዳ ሕዝብ እንዲተባበራቸው ፈለጉ፤ አካዝ ግን አሻፈረኝ አለ። በዚህ ምክንያት ሶርያና እስራኤል በይሁዳ ላይ ጥቃት ፈጸሙ። አካዝ እነዚህን አገሮች እንዳይፈራቸውና በእግዚአብሔር እንዲታመን ኢሳይያስ ቢነግረውም፥ መልእክት ወደ አሦር በመላክ እንድታድነው ጠየቀ። አሦር ሶርያን በማጥቃት በ732 ዓ.ዓ. ሙሉ ለሙሉ አጠፋቻት። የእስራኤልንም ምድር በአብዛኛው በመውሰድ መንግሥቱን አስገበረች። የአሦር ንጉሥ በሞተ ጊዜ ግን እስራኤል ከሌሎች ብዙ አሕዛብ ጋር በመሆን ለማመፅ ወሰነች። አሦር በ722 ዓ.ዓ. እስራኤልን በመደምሰስ አብዛኛውን ሕዝብ በምርኮ ወሰደች።

ኢሳይያስ የእስራኤልን ጥፋት ያየው በከፍተኛ ኃዘን እንደነበር ጥርጥር የለውም። እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል ቢሆኑም፥ ኃጢአታቸው ጥፋትን አመጣባቸው። ኢሳይያስ ወደፊት ይሁዳም የሰሜኑ መንግሥት ያደረገውን ይህንኑ ኃጢአት በማድረግ ወደ ምርኮ እንደምትሄድ በተጨማሪ ያውቅ ነበር።

6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለ ኃጢአታቸው ሲቀጣቸው ያየኸው በምን መንገድ ነው? ለ) ይህ ቅጣት እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ላይ ታላቅ ሥቃይ የሚያስከትለው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት በራሱ ሕዝብ ላይ ፍርድን ሲያመጣ እርሱን የሚፈሩ ሰዎች ምላሽ ምን መሆን አለበት?

አካዝ አሦር ባደረገችው ነገር በጣም ተደስቶ ነበር። የአምላካቸውን (የጣዖታቸውን) ምስል ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በማምጣት፥ ሕዝቡ የአሦራውያንን አምላክ እንዲያመልኩ አዘዘ። ሕዝቡ እውነተኛውን አምላክ እንዲያመልኩ አልፈቀደላቸውም። ኢሳይያስ ይህ ጉዳይ

በእስራኤል ላይ ያመጣውን ዓይነት ፍርድ በይሁዳ ሕዝብም ላይ ሊያስከትል እንደሚችል ተገንዝቦ ነበር። የትንቢተ ኢሳይያስ መጀመሪያ ክፍል አብዛኛው ምዕራፍ በአካዝ የክፋት ዘመን መንግሥት የተጻፈ ነው (ለምሳሌ፡- ኢሳይያስ 9)።

4. ሕዝቅያስ፡- የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን የሚፈራና መንገዱን ከጌታ ጋር ያደረገ ንጉሥ ነበር። ኢሳይያስ ከሕዝቅያስ ጋር በቅርብ ሳይሠራ አልቀረም። እስራኤል ከወደቀችና ሕዝቅያስ ከነገሠ በኋላ ሕዝቡ በቤተ መቅደስ ውስጥ እውነተኛውን አምላክ ማምለክ እንዳለባቸው ወሰነ። በወደቀው የእስራኤል መንግሥትና በይሁዳ መንግሥት ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን በቤተ መቅደሱ ያመልኩ ዘንድ ጋበዘ። በይሁዳ መንግሥት ውስጥ በርካታ መንፈሳዊ ተሐድሶ አካሄደ። ይሁን እንጂ ከአሦር በኩል በይሁዳ ላይ እንደገና ችግር ተነሣ። ዳግማዊ ሳርጎን የተባለ አዲስ ንጉሥ (ከ722-705 ዓ.ዓ.) ሥልጣን ከያዘ በኋላ፥ ፍልስጥኤምንና (711 ዓ.ዓ.) በአሦር ላይ የተባበሩ ሌሎች ሕዝቦችን ሁሉ ወጋ። በዚህ ነገር እንዳይተባበር ኢሳይያስ ሕዝቅያስን አስጠንቅቆት ነበር። ኢሳይያስ ለሦስት ዓመታት እንደ ባሪያ ያለጫማ በመሄድና ቡቱቶ ለብሶ በመመላለስ ግብፅና ተባባሪዎችዋ እንዴት ለአሦር ባሪያዎች እንደሚሆኑ አሳይቷል። ሕዝቅያስ ለአሦር እንዲገብር ቢገደድም እንኳ ኢየሩሳሌም ጥቃት አልደረሰባትም። ሳርጎን በሞተ ጊዜ ግን ሕዝቅያስ የአሦርን የበላይ ጭቈና አሽቀንጥሮ ለመጣል ተፈተነ። የግብፅ ሕዝብ አሦርን ለመጣል የሚችል የጎብረ-ብሔር ጦር ለማቋቋም የሞከረው በዚህ ጊዜ ነበር። ኢሳይያስ፥ ሕዝቅያስን ወደዚህ ጎብረት በመግባት በግብፅ እንዳይታመን አስጠነቀቀው። ይልቁንም በእግዚአብሔር እንዲታመን አበረታታው። አሦር በሰናክሬም መሪነት ይሁዳን በመውጋት አብዛኛውን የይሁዳ ክፍል ደመሰሰ። ሆኖም ኢሳይያስ አስቀድሞ እንደተናገረው፥ እግዚአብሔር የአሦርን ጦር በመደምሰስ (በ701 ዓ.ዓ.) ኢየሩሳሌምን ከጥፋት ጠበቃት።

5. ምናሴ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢሳይያስ አሟሟት ባይነግረንም እንኳ የአይሁድ አፈ- ታሪክ በምናሴ ዘመነ መንግሥት በመሥዋዕትነት መሞቱን ይናገራል። ምናሴ በአብዛኛው የሕይወት ዘመኑ እግዚአብሔርን እንደተወና የጣዖት አምልኮን ሥርዓት እንደገና ወደ

ይሁዳ እንዳመጣ ታስታውሳለህ። ኢሳይያስ ይህን በሚመለከት እንደተቃወመው ጥርጥር የለውም። የአይሁድ አፈ ታሪክ እንደሚናገረው፥ ኢሳይያስ በአንድ ውስጠ ክፍት በሆነ የዛፍ ግንድ ውስጥ ከምናሴ በተሸሸገ ጊዜ፥ ምናሴ በመጋዝ ለሁለት እንደሰነጠቀው ይናገራል (ዕብራውያን 11፡37 ተመልከት።)

---

7ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ የኖረበትን ዘመን ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ገጽታ በአንድ ዐረፍተ ነገር ግለጥ። (ኢሳይያስ ስለኖረበት ጊዜ ማወቅ አብዛኛውን ትንቢቶቹን ለመረዳት ይጠቅምሃል።)

---

እርግጠኛ ለመሆን ባንችልም እንኳ አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት፥ ትንቢተ ኢሳይያስ የተጻፈው ቀጥለው በተጠቀሱት ነገሥታት የግዛት ዘመን ቅደም ተከተል ነው፡-

1. ኢሳይያስ 1-6 የተጻፈው በዖዝያንና በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት ነው (740-735) ዓ.ዓ.)፤
2. ኢሳይያስ 7-12 በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተጻፈ ነው (735-715 ዓ.ዓ.)፤
3. ኢሳይያስ 13-39 የተጻፈው ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት ከመነሣቱ በፊት፥ በሕዝቅያስ የመጀመሪያ ዘመነ-መንግሥት ነበር፤ (715-701 ዓ.ዓ.)፤
4. ኢሳይያስ 40-66 በሕዝቅያስ የኋለኛ ዘመነ መንግሥትና በምናሴ የመጀመሪያ ዘመነ መንግሥት የተጻፈ ነው (701-680 ዓ.ዓ.)።

## 2. የነቢዩ ኢሳይያስ ሥረ- መሠረት

8ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ የሚለውን ስም በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከትና ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ የተጻፉ አንዳንድ እውነቶችን ጥቀስ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢሳይያስ የግል ሕይወት የሚነግረን ብዙ ነገር የለም፤ ሆኖም ስለ እርሱ የሚከተሉትን መሠረታዊ እውነቶች እናውቃለን፡-

1. ኢሳይያስ የአሞጽ ልጅ ነበር። የአይሁድ አፈ- ታሪክ አሞጽ የንጉሥ ዖዝያን አባት የነበረው የንጉሥ አሜስያስ ወንድም ነው ይላል። ይህ ማለት ንጉሥ ዖዝያንና ኢሳይያስ የአጎት ልጆች ናቸው ማለት ነው፤ ስለዚህ ኢሳይያስ የዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ አካል የነበረ፥ ብዙ መብትና ዕድል የነበረው ሰው ነው። ኢሳይያስ ለንጉሥ አካዝና ሕዝቅያስ በቀጥታ ይናገር የነበረበት ምክንያት ዘመዶቹ ስለነበሩ ይሆናል። ምናልባት በሃይማኖትም ሆነ በፖለቲካ ትምህርት የሠለጠነ ሰው ሳይሆን አይቀርም።

2. ኢሳይያስ እንደ እርሱ ነቢይት የሆነች ሴት አግብቶ ነበር (ኢሳይያስ 8፡3)። የኢሳይያስ ሚስት ነቢይት መሆኗን በሁለት የተለያዩ መንገዶች መገንዘብ እንችላለን፤ ይኸውም፡- አንድም ልክ እንደ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቃል በመናገር በእርግጥ የነቢይነትን ሥራ የምትሠራ ነበረች ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ነቢይ ስላገባች ነቢይት ተብላ ተጠርታ ሊሆን ይችላል።

3. ለኢሳይያስ ቢያንስ ሁለት ልጆች እንደነበሩት እናውቃለን። እነዚህ ሁለት ልጆቹ የእርሱን የነቢይነት መልእክት የሚያንጸባርቁ ልዩ የሆኑ ስሞች ነበሯቸው። የአንዱ ልጅ ስም በዕብራይስጥ ማሃር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ ሲሆን፥ ትርጕሙ «ምርኮ ፈጠነ፥ ብዝበዛ ቸኮለ» ማለት ነው። ይህ ስም እስራኤላውያን ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው ካልተመለሱ እግዚአብሔር ለሚግርኩአቸው አሕዛብ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው የሚናገር የማስጠንቀቂያ መልእክት ነበር (ኢሳይያስ 8፡1-3)።

የሁለተኛው ልጅ ስም በዕብራይስጥ ሸአር-ያሹብ ሲሆን ትርጕሙም «ቅሬታዎቹ ይመለሳሉ» ማለት ነው። ይህ ስም እስራኤላውያንን ለማጽናናትና ለማበረታታት የተሰጠ ስም ነበር። እግዚአብሔር እንደሚያስማርካቸው የተናገረ ቢሆንም፥ ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋቸው ግን አልነበረም። ሁልጊዜ ለእርሱ የሆኑ ቅሬታዎች ነበሩት፤ ስለዚህ አንድ ቀን እግዚአብሔር እነዚህን ቅሬታዎች በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ወደ ይሁዳ ሊመልሳቸው ተስፋ ሰጠ (ኢሳይያስ 7፡3)።

አንዳንድ ምሁራን ኢሳይያስ ሌሎች ሁለት ተጨማሪ ልጆች ነበሩት ብለው ያምናሉ። የአንዱ ስም «አማኑኤል» ሲሆን የሌላኛው ስም ግን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም ይላሉ። [ኢሳይያስ 7፡14፤ 8፡8፥ 10፤ 9፡6]።

4. ኢሳይያስ አገልግሎት የሰጠው ብቻውን ሆኖ አልነበረም። ኢሳይያስ በሠራበት ዘመን ሆሴዕና አሞጽ በሰሜን እስራኤል ያገለግሉ ነበር። ሚክያስ ደግሞ በይሁዳ ገጠር ክፍል ያገለግል ነበር። የሚክያስና የኢሳይያስ መልእክቶች ምን ያህል ተመሳሳይ እንደሆኑ ማየት የሚያስደንቅ ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ መልእክቶቻቸው ፍጹም ተመሳሳይ ነበሩ (ለምሳሌ፡- ኢሳይያስ 2፡1-4ን ከሚክያስ 4፡1-3 ጋር አወዳድር)። መልእክቶቻቸው የተመሳሰሉት ኢሳይያስ ለይሁዳ መሪዎች የሰጠውን መልእክት ሚክያስ በገጠር ላሉ ሰዎች በድጋሚ ስለተናገረ ሳይሆን አይቀርም።

5. ኢሳይያስ የተነበየው ስለ ሁለቱም ግለት ስለ ደቡቡና ሰሜኑ መንግሥታት ቢሆንም ዋናው መልእክቱ ስለ ይሁዳና እርሱ ስለኖረባት ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ ነበር።

## የትንቢተ ኢሳይያስ አስተዋጽኦ

እንደ አብዛኛዎቹ የትንቢት መጻሕፍት ሁሉ የትንቢተ ኢሳይያስንም አስተዋጽኦ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍሎች ዝርዝር ጉዳዮችን ያላካተቱ ተከታታይ መልእክቶችና ትንቢቶች ናቸው። ኢሳይያስ ከፍርድ መልእክት አጽናኝና ተስፋ ሰጭ ወደሆነ መልእክት፥ እንደገና ደግሞ ወደ ፍርድ መልእክት የሚመላለስ ይመስላል። ይህ ዑደት በመጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ ሲፈጸም የሚታይ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ከመጽሐፉ አስተዋጽኦ ውስጥ አንዱ ሊሆን ይችላል።

> 9ኛ ጥያቄ፥ የሚከተለውን የትንቢተ ኢሳይያስ አስተዋጽኦ የመጽሐፉን ዋና ዋና ክፍሎችና በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ዐበይት ትምህርቶች አጠቃላይ ገጽታ ለማግኘት በሚያስችል መንገድ አጥና።

## ክፍል 1፡- በእስራኤል፥ በይሁዳና በአሕዛብ ሁሉ ላይ የመጣ የፍርድ መልእክት መጽሐፍ (ኢሳይያስ 1-39)

1. የትንቢተ ኢሳይያስ መግቢያ-እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚደርሰው ነገርና በወደፊት ሁኔታቸው ሉዓላዊ ነው (ኢሳይያስ 1-6)፡-

ሀ. ይሁዳ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገችውን ቃል ኪዳን በማፍረሷ እንደተወቀሰች (ኢሳይያስ 1)፥

ለ. እግዚአብሔር ወደፊት የሚመሠርተው መንግሥት (ኢሳይያስ 2፡1-5)፥

ሐ. እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ (ኢሳይያስ 2፡6-4፡1)፥

መ. ስለ ይሁዳ የወደፊት ተሐድሶ (ኢሳይያስ 4፡2-6)፥

ሠ. እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ የሰጠው ፍርድና የሚመጣው ምርኮ (ኢሳይያስ 5)፥

ረ. የኢሳይያስ ራእይና ለነቢይነት መጠራቱ (ኢሳይያስ 6)።

2. በአንድ ሕዝብ ላይ አገር አቀፍ የሆነ መከራና ችግር በሚደርስበት ጊዜ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው-እስራኤልና ሶርያ ይሁዳን በወረሩበት ወቅት የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 7-12)፡-

ሀ. ይሁዳ በእስራኤልና በሶርያ እጅ እንደማትወድቅ በመግለጽ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 7)፡-

ለ. ስለ ኢሳይያስ ወንድ ልጆችና የዳዊት ልጅ ስለሆነው ስለ መሢሑ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 8-9፡7)፥

ሐ. የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ (ኢሳይያስ 9፡8-10፡4)፥

መ. የእግዚአብሔር ፍርድ በአሦር ላይ (ኢሳይያስ 10፡5-34)፥

ሠ. መሢሑና የወደፊት መንግሥቱ (ኢሳይያስ 11-12)።

3. እግዚአብሔር በሕዝቦች ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ነው-በተለያዩ ሕዝቦች ላይ የተነገሩ ትንቢቶች (ኢሳይያስ 13-23)፡-

ሀ. በአሦር ላይ (ኢሳይያስ 13፡1-14፡27)፥

ለ. በፍልስጥኤም ላይ (ኢሳይያስ 14፡28-32)፥

ሐ. በሞዓብ ላይ (ኢሳይያስ 15-16)፥

መ. በደማስቆና በእስራኤል ላይ (ኢሳይያስ 17)፥

ሠ. በኢትዮጵያ ላይ (ኢሳይያስ 18)፥

ረ. በግብፅና በኢትዮጵያ ላይ (ኢሳይያስ 19-20)፥

ሰ. በባቢሎን ላይ (ኢሳይያስ 21፡1-10)፥

ሸ. በኤዶም ላይ (ኢሳይያስ 21፡11-12)፥

ቀ. በዐረብ ላይ (ኢሳይያስ 21፡13-17)፥

በ. በኢየሩሳሌም ላይ (ኢሳይያስ 22)፥

ተ. በጢሮስ ላይ (ኢሳይያስ 23)።

4. እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝቡ ላይ ሉዓላዊ ነው-ስለ ፍርድና ስለሚመጣው መንግሥት የተተነበዩ የተስፋ ቃላት (ኢሳይያስ 24-27)።

5. እግዚአብሔር በፍርድ ላይ ሉዓላዊ ነው-በእስራኤልና በአሦር ላይ የተነገሩ ስድስት የዋይታ ትንቢቶች (ኢሳይያስ 28-33)።

6. እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው-የፍርድ መልእክቶችና የበረከት ተስፋዎች (ኢሳይያስ 34-35)።

7. እግዚአብሔር በዓለም ላይ ባሉ ታላላቅ ኃያላን ላይ ሉዓላዊ ነው-እግዚአብሔር ነፃ እንደሚያወጣ የተነገረ ታሪክና ወደፊት ይሁዳ በባቢሎን እንደምትማረክ የተነገረ ትንቢት (ኢሳይያስ 36-39)።

## ክፍል 2፡- የማጽናናት መጽሐፍ (ኢሳይያስ 40-66)

8. በአይሁድ ሕዝብ ነፃ መውጣትና መመለስ ላይ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው (ኢሳይያስ 40-48)።

9. አገልጋይን ወደ ሕዝቡ በመላክ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው (ኢሳይያስ 49-57)።

10. በመጨረሻዎቹ ዘመናት ጉዳይ፥ ሕዝቡን ነፃ በማውጣት፥ በክፉዎችና በኃጢአተኞች ላይ በመፍረድና ሊመጣ ባለው ዘላለማዊ መንግሥት ጉዳይ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው (ኢሳይያስ 58-66)

---

10ኛ ጥያቄ፥ ከላይ በተሰጠው አስተዋጽኦ ላይ የተንጸባረቁ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚፈለጉባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

---

## 2ኛ ቀን፡ - የትንቢተ ኢሳይያስ ዓላማና ትምህርት

### የትንቢተ ኢሳይያስ ዓላማ

የትንቢተ ኢሳይያስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ ጥልቅ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች መካከል አንዳንዶቹን የያዘ ነው። መጽሐፉ የይሁዳ ሕዝብ በባቢሎን መንግሥት የሚማረክበትን ምክንያትና የይሁዳ ሕዝብ ቅሬታ ደግሞ በመጨረሻ ከምርኮ እንደሚመለስ ቢናገርም፥ የመጽሐፉ ተቀዳሚ ትኩረት ግን ይህ አይደለም። የኢሳይያስ ትኩረት በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ነው። የቀሩት ትምህርቶች በሙሉ ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር የነበረው ግንዛቤ ውጤቶች ናቸው። እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ እንደሚፈርድ ኢሳይያስ የሰጠው የማስጠንቀቂያ መልእክት የተመሠረተው በእግዚአብሔር ቅድስናና በሕዝቡ መካከል በሚከሠት ኃጢአት ላይ እንደሚፈርድ አስቀድሞ በሰጠው ቃል ኪዳን ላይ ነው። ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የሚቆዩ ቅሬታዎች እንደሚኖሩ የተሰጠው ማረጋገጫ ወይም ዋስትና ደግሞ እግዚአብሔር ለገባው የተስፋ ቃል ያለውን ታማኝነት የሚያሳይ ነው። ስለ ሕዝቦች መሸነፍ የሚናገሩት ትንቢቶች ደግሞ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ሁሉ በበላይነት እንደሚቆጣጠርና ሉዓላዊ መሆኑን የሚያንጸባርቁ ናቸው። እግዚአብሔር ብቻውን በሚነግሥበት ጊዜ የሚኖረውን ወርቃማ ዘመንና ሰላም በምድር ላይ መስፈን የሚያሳየው፥ ንጉሥነቱንና በምድር ላይ ያለውን ዓላማ በመፈጸም መንግሥቱን እንደሚመሠርት ነው። በዚህ መንግሥት ጽድቅ ይኖራል፤ ደግሞም አይሁድም ሆኑ አሕዛብ እግዚአብሔርን ያመልኩታል።

> 11ኛ ጥያቄ፥ በኢትዮጵያ የሚገኙ ክርስቲያኖችም ይህን ዓላማ በሚገባ መረዳት የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው?
> 12ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር በነቢይ በኩል ዛሬ ለኢትዮጵያ ቢናገር ናሮ የሚሰጠው መልእክት ምን ዓይነት የሚሆን ይመስልሃል? ለምን?

ነቢይ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ወይም ቃል አቀባይ መሆኑን ተመልክተናል። በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች እንዲያደርስ እግዚአብሔር ግልጽ የሆነ መልእክት ይሰጠው ነበር። መልእክቱ ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ነቢዩ የነበረበትን ዘመን ነው። ይኸውም ሊመጣ ስላለው ፍርድ

ማስጠንቀቂያ ወይም ተግሣጽ የሚሆን ወይም እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግላቸው የሚናገር የተስፋ መልእክት ነበር። አንዳንድ ጊዜ መልእክቱ ወደፊት የሚፈጸምን ነገር ያመለክት ነበር። በዚያን ዘመን ለነበሩ እስራኤላውያን በቅርቡ የተፈጸመ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ገና ወደፊት በዘመናት መጨረሻ የሚፈጸም ትንቢት ሊሆን ይችላል።

ኢሳይያስ ከ740-680 ዓ.ዓ. ለይሁዳ ሕዝብ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ነበር። ኢሳይያስ ታላቅ ነቢይ የነበረ ቢሆንም፥ መልእክቱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ለመመለስ እስከዚህም ስኬታማ አልነበረም። ትንቢተ ኢሳይያስን ለመረዳት ከምዕራፍ 6 መጀመር አለብን። ይህ ክፍል ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ነቢይ እንዲሆን እንዴት እንደተጠራ የሚያሳይ ነው። ይህ ጥሪ በ740 ዓ.ዓ. ለኢሳይያስ ደረሰውና ሕይወቱን ለወጠው። አብዛኛዎቹ የትንቢተ ኢሳይያስ ኃለኛ መልእክቶች የሚያንጸባርቁት እርሱ በተጠራ ጊዜ ምን እንደተማረ ነው።

> 13ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 6 አንብብ። ሀ) ኢሳይያስ ያየው ራእይ ምን ነበር? በዚህ ራእይ ውስጥ የታዩት የእግዚአብሔር ዐበይት ባሕርያት ምንድን ናቸው? ለ) ኢሳይያስ ስለ ራሱና ስለ እስራኤላውያን ሕይወት ከዚህ ራእይ የተገነዘበው ምንድን ነው? ሐ) የኢሳይያስ መልእክት ምን መሆን ነበረበት? መ) ለኢሳይያስ ሥራ የተሰጠው ምላሽ ምን ነበር? ሠ) በሕዝቡ ላይ ምን ሊደርስ ነበር? (ቊጥር 11-13)።

ኢሳይያስ 6 የሚያንጸባርቀው የትንቢተ ኢሳይያስን ዋና ዋና ትምህርቶችን ነው። በኢሳይያስ 6 የሚከተሉትን ዋና ዋና ትምህርቶችን መመልከት እንችላለን፦

1. የእግዚአብሔር ታላቅነትና ቅድስና (6፡1-4)፦ እነዚህን ሁለት የእግዚአብሔር ባሕርያት በመጽሐፉ በአጠቃላይ ያለማቋረጥ በተደጋጋሚ የምናያቸው ናቸው። በመጀመሪያ፥ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ታላቅነት «በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ» አየ። በዚህ ዓይነት ትንቢተ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን የሰዎች ሁሉ ንጉሥ ወይም ገዥ አድርጎ ያለማቋረጥ ያቀርበዋል። እግዚአብሔር በሰማይ በዙፋኑ ላይ ሆኖ በምድር የሚፈጸሙ ድርጊቶችንና አካሄድን ይመራል። በሕዝቦች ላይ ይገዛል፤ ድርጊቶቻቸውንም ሁሉ

ይቆጣጠራል። ኃይሉና ጥበቡ እጅግ ከፍተኛና የላቀ በመሆኑ፥ ሊቋቋመው የሚችል ማንም የለም።

ሁለተኛ፥ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ያየው በቅዱስነቱ ነው። ሱራፌልም ያለማቋረጥ ይህንን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያውጁ ነበር።

14ኛ ጥያቄ፥ «ቅዱስ» ማለት ምን ማለት ነው? ይህንን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ቅዱስ» የሚለው ቃል መሠረታዊ ትርጉም «መለየት» ማለት ነው። «መለየት» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁለት ነገሮችን ነው፤ በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ከተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ የተለየ መሆኑን ያመለክታል። እርሱ ከተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ የተለየና የላቀ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ «ቅዱስ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው፥ እግዚአብሔር ከኃጢአት የተገለለ መሆኑን ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚፈርደው ቅዱስ ስለሆነ ነው።

በትንቢተ ኢሳይያስ፥ ነቢዩ እግዚአብሔርን የሚጠራበት የተለየ ስም አለው። ኢሳይያስ እግዚአብሔርን «የእስራኤል ቅዱስ» ብሎ ይጠራዋል፤ ይህም ስም 26 ጊዜ በመጽሐፉ ውስጥ ተጽፎ እናየዋለን። ስለሆነም፥ በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ በአጠቃላይ በግልጽ እንደምናየው፥ የመጽሐፉ ትኩረት በእግዚአብሔር ቅድስና፥ በኃጢአት ላይ በሚገልጸው ቊጣና ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ባለው ውሳኔ ላይ ነው። ይህም የራሱን ሕዝብ እስራኤልንና ይሁዳን፥ ደግሞም አሕዛብን በመቅጣቱ ታይቷል።

2. የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአተኝነት (6፡5-7)፡- ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቅድስና በተመለከተ ጊዜ ወዲያውኑ የተገነዘበው ነገር እርሱና ሕዝቡ ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደሆኑ ነበር። የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚያሳይ ራእይ ሁልጊዜ የሚያስገነዝበን የራሳችን ኃጢአት ከፍተኛነት ነው።

15ኛ ጥያቄ፥ የእግዚአብሔርን ቅድስና ይበልጥ በተረዳን ቊጥር የራሳችንን ኃጢአተኝነት በበለጠ በመገንዘብ ያዳነንንና የወደደንን እግዚአብሔርን እንዴት አብልጠን ልናደንቀውና ልናከብረው እንደሚገባን ግለጽ።

የትንቢተ ኢሳይያስ አብዛኛው ክፍል የሚያተኩረው በፍርድ ላይ ነው። ይህ ፍርድ እግዚአብሔርን በካዱ ሕዝቦች ሁሉ ላይ ይመጣል። ነገር ግን ይህ ፍርድ በተለይ የሚመጣው የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ በሆኑት በአይሁድ ላይ ነው። ኢሳይያስ ይህ ፍርድ የሚመጣበትን ምክንያት ይናገራል። ይህ ፍርድ የሚመጣው በእግዚአብሔር ማንነት ምክንያት ነው። እርሱ ክፉዎችን የሚቀጣ ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ ነው። ፍርዱ የሚመጣው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕግጋቱን በግልጽ በመቃወማቸው፥ ለሰዎች ቅን ፍርድን በመንፈጋቸው፥ በመታበያቸው፥ ወዘተ. ነው።

16ኛ ጥያቄ. ፥ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውና ሥራዎቻቸው ሁሉ እንደሚፈረዱና ፍርድ እንደሚሰጥ (እንደሚፈተኑ) በማወቅ መኖር ያለባቸው እንዴት ነው? (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡10-15 ተመልከት)።

3. የኢሳይያስ መልእክት ተገቢውን ምላሽ ማጣቱ (6፡9-10)፡- ኢሳይያስ መልእክቱን ለማስተላለፍ ከተዘጋጀበት ከመጀመሪያው አንሥቶ ማንም እንደማይሰማው እግዚአብሔር ነግሮት ነበር። ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ኢሳይያስ ያለማቋረጥ ቢለምንም፥ ሕዝቡ ግን አልተቀበሉትም። ኃጢአታቸው የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት የማይሹ ልበ-ደንዳናዎች አድርጎአቸው ነበር። ዓለማዊ በሆነ ምርጫቸው ረክተው ነበርና የያዙትን ለመለወጥ አይፈልጉም ነበር። አይሁዶች ሃይማኖታውያንና እግዚአብሔርን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ያመልኩ የነበሩ ሰዎች ቢሆኑም፥ እግዚአብሔርን ከልባቸው የሚያመልኩ ወይም ከእነርሱ ጋር በሲና ተራራ ላደረገው ቃል ኪዳን በመታዘዝ የሚኖሩ ሰዎች አልነበሩም።

17ኛ ጥያቄ፥ ይህ ተመሳሳይ ነገር ዛሬም ቢሆን በክርስቲያኖች የሚፈጸመው እንዴት ነው? አንዳንድ መግለጫዎችን ስጥ።

4. የእግዚአብሔር ሕዝብ በንስሐ ስለማይመለስ እግዚአብሔር በሕዝቡና በከተማዋ ላይ ጥፋትን እንደሚያመጣ ተናግሯል (6፡11-13)። በትንቢተ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ተናግሯል። እስራኤል በሙሉ ተማርከው ወደ አሦር ተጋዙ። ኢሳይያስ፥ ይሁዳም

ተማርካ ወደ ባቢሎን እንደምትሄድ ተናገረ። በኢሳይያስ የአገልግሎት ዘመን፥ ይህ የፍርድ ተስፋ ቃል አሦራውያን አብዛኛውን የይሁዳ ክፍል በመደምሰሳቸው ምክንያት በከፊል ተፈጽሟል። ሆኖም እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ታድጎአታል።

5. እግዚአብሔር ይሁዳን የሚያጠፋው ሙሉ በሙሉ አልነበረም፤ ነገር ግን የቀረው ጉቶ «የተቀደሰ ዘር» ይሆናል (6፡13)። ይህ ሐረግ የሚገልጸው ኢሳይያስ ስለ ይሁዳ ቅሬታ የሚያስተምረውን ነገር ነው። አብዛኛው ሕዝብ ቢጠፋ ወይም በምርኮ ቢጓዝም፥ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለእርሱ ታማኝ ሆነው የሚቀሩ «ቅሬታዎች» ይኖሩታል። እነዚህ ቅሬታዎች አንድ ቀን ወደ ይሁዳ ይመለሳሉ። እግዚአብሔር አንድ ቀን መንፈሱን የሚያፈስሰውና መንግሥቱንም የሚያመጣው በዚህ ቅሬታ ላይ ነው።

በዚህ የኢሳይያስ ራእይ የተካተተው ሌላው ዐቢይ ትምህርት እግዚአብሔር በዘመናት መጨረሻ የሚያመጣው የዘላለም መንግሥት ነው። ትንቢተ ኢሳይያስ በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ የትንቢት መጻሕፍት ሁሉ ይልቅ እግዚአብሔር ለዘላለም ስለሚነግሥበት ዘላለማዊ መንግሥት ይገልጻል።

## በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና አሳቦች

ትንቢተ ኢሳይያስን በምታነብበት ጊዜ፥ የሚከተሉትን ዋና ዋና አሳቦች መመልከት ጠቃሚ ነው። እነዚህ ዐበይት ዋና አሳቦች ሌሎች ትንቢቶችና ትምህርቶች የተመሠረቱባቸው የመጽሐፉ የጀርባ አጥንት ተደርገው የሚታዩ ናቸው።

1. የእግዚአብሔር ባሕርይ፡- ትንቢተ ኢሳይያስ ከሌሎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፥ በተፈጥሮ፥ በሕዝቦችና በመንግሥታት ላይ ያለውን የበላይ ተቆጣጣሪነትን የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። ይህ ባሕርይ ታላቅነትና ግርማን፥ ፍቅርና ምሕረትን፥ ፍርድና ቁጣን፥ ይቅርታና ተሐድሶን የሚጨምር ነው። እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት እንደተገለጠ ተመልከት።

| 18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ማንነት ግልጽና ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? |
|---|

ለ) ይህ ነገር እንዴት ሊያበረታታቸው ይችላል? ሐ) እግዚአብሔርን በትሕትና ለማገልገል ይህ ሊረዳቸው የሚችለው እንዴት ነው?

2. እግዚአብሔር የእስራኤል ቅዱስ ነው፡- ኢሳይያስ በመጽሐፉ እግዚአብሔርን ለመጥራት የተጠቀመባቸው የተለያዩ ስሞች ቢኖሩትም፥ አንድ ልዩ የሆነ ስም ግን ነበረው፤ ያም ስም «የእስራኤል ቅዱስ» የሚል ነው። በሌሎች ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አልፎ አልፎ ከመጠቀሱ በቀር፥ ይህ የእግዚአብሔር ስም የሚገኘው በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ብቻ ነው። ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ያተኩራል፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ቅዱስ ብሎ ቢጠራቸውም እንኳ ከሕዝቡ ኃጢአተኝነት ጋር በንጽጽር የቀረበ ነው።

19ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ጴጥ. 1፡15-16 አንብብ። ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር ሲነጻጸር የክርስቲያን ኃላፊነት ምንድን ነው?

3. እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያዋርዳል (ኢሳይያስ 2፡11-17)፡- በእዚህ ስፍራ ትዕቢተኞች የተባሉት ሀ) ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ተቃራኒ ሆነው የቆሙ ሕዝቦች፥ ለ) ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑ የይሁዳ ወይም የሌሎች ሕዝቦች ነገሥታት ወይም ሐ) በታዛዥነት ሕይወታቸውን እግዚአብሔርን ለመስጠት ፈቃደኞች ባለመሆን ትዕቢተኝነታቸውን የሚገልጡ ማንኛቸውም ተራ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር ትዕቢትን ስለሚጠላ ይፈርድበታል።

20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ትዕቢትን በእነዚህ ሦስት የሕይወት ክፍሎች ያየኸው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ሲያዋርድ ያየኸው እንዴት ነው? ሐ) ይህ በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዳይታበዩ ማስጠንቀቂያ መሆን ያለበት እንዴት ነው?

4. እግዚአብሔር እስራኤልን የሚቤዥ ነው፡- እግዚአብሔር አይሁድን በኃጢአታቸው ምክንያት ተግርከው እንዲሄዱና ለአሕዛብ መንግሥት ባሪያዎች እንዲሆኑ ቢያደርግም፥ የሚቤዣቸውም ራሱ እግዚአብሔር ነው (ኢሳይያስ 41፡14፤ 43፡14፤44፡6 ተመልከት)።

5. እግዚአብሔር ባዕዳን መንግሥታትን ይቆጣጠራል፡- በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ያለማቋረጥ የምናየው እግዚአብሔር በአጠቃላይ የአሕዛብ ሁሉ ተቆጣጣሪ መሆኑን ነው። ሕዝቡን ለመቅጣት አሦራውያንን ያስነሣው እግዚአብሔር ነው። የይሁዳን ሕዝብ ለማጥፋት ባቢሎንን ያስነሣው እግዚአብሔር ነበር። ባቢሎንን ለማጥፋትና የይሁዳን ሕዝብ ወደ እስራኤል ለመመለስ የእግዚአብሔር «አገልጋይ» የሆነውን ቂሮስን የተጠቀመበት እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር አንድን ሕዝብ ከፍ ያደርጋል፤ ሌላውን ያዋርዳል። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ በሚያምፁት አሕዛብ ሁሉ ላይ ይፈርድባቸዋል።

6. የእስራኤል ቅሬታዎች፡- ትንቢተ ኢሳይያስ ካተኮረባቸው ነገሮች አንዱ ቅሬታዎችን የሚመለከት ነው። በኤልያስ ዘመን ለበኣል ያልሰገዱ 7000 ሰዎች እንደነበሩ ሁሉ (1ኛ ነገሥት 19፡18)፥ እግዚአብሔር ምንጊዜም ለእርሱ ታማኞች የሆኑ ቅሬታዎች አሉት። እግዚአብሔር እነዚህን ቅሬታዎች ነፃ ለማውጣትና ለግዳን ደግሞም ወደ ይሁዳ ምድር ለመመለስ ቃል ገብቶላቸው ነበር። ኢሳይያስ ለእነዚህ ቅሬታዎች የሚጽፍላቸው የማበረታቻ መልእክት ታላቅ ጥፋት በሚሆንበት ጊዜ እንኳ ለእግዚአብሔር ታማኞች እንዲሆኑ የሚያሳስብ ነበር። በእምነታቸው ጸንተው ቢቆዩና ለእግዚአብሔር ቢታዘዙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሽልማትን ያገኛሉ።

7. ስለ እስራኤል ሕዝብ ተሐድሶ፡- እግዚአብሔር በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ፍርድን እንደሚያመጣ አስቀድሞ የተናገረ ቢሆንም ከምርኮ እንደሚመልሳቸውም አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ዕቅድ ነበረው።

8. በይሁዳ ላይ ገዥ የሚሆነው የመሢሑ መምጣት፡- በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት መጻሕፍት ሁሉ በላቀ ሁኔታ ትንቢተ ኢሳይያስ በመሢሑ መምጣት ላይ ትኩረት ያደርጋል። መሢሑ ንጉሥ ሆኖ ሊገዛ ከዳዊት የዘር ግንድ ይመጣል። ከድንግል ይወለዳል፤ ነገር ግን አማኑኤል ይሆናል። በሰዎች መካከል በሥጋ የሚኖር በባሕሪው ግን እግዚአብሔር ማለት ነው። በቤተልሔም ተወልዶ፥ በገሊላ ያገለግላል። የገዛ ወገኖቹ ይገድሉታል፤ እርሱ ግን ከኃጢአታቸው

ያድናቸዋል። እነዚህ ስለ መሢሑ ከተነገሩ ትንቢቶች ጥቂቶቹ ናቸው። አዲስ ኪዳን ከማንኛውም የትንቢት መጻሕፍት ይልቅ ከትንቢተ ኢሳይያስ ይጠቅሳል።

9. የእግዚአብሔር አገልጋይ፡- በትንቢተ ኢሳይያስ ሁለተኛ ግማሽ ክፍል ካሉት ልዩ አሳቦች አንዱ «የአገልጋይ መዝሙራት» ወይም ልዩ ስለሆነው የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚናገረው መዝሙር ነው (ኢሳይያስ 42፡1-7፤ 49፡1-9፤ 52፡13-53፡12፤ 61፡1-3)። እስራኤል የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆነች የተጠቀሰ ቢሆንም፥ እነዚህ ክፍሎች የሚናገሩት ግን ስለ አንድ ልዩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው። እስራኤል ፈቃዱን የምትፈጽም አገልጋዩ እንድትሆን እግዚአብሔር የመረጣት ቢሆንም፥ እርስዋ ግን አልቻለችም። ሆኖም እግዚአብሔር ፈቃዱን ሙሉ በሙሉ የሚፈጽምና ታዛዥ የሆነ ልዩ አገልጋይ ነበረው፤ እርሱም መሢሑ ነበር። ስለ እስራኤል ሕዝብ ኃጢአት የሚሞትና የሚፈውሳቸው ይህ መሢሕ ነው። ከአዲስ ኪዳን በግልጽ እንደምንረዳው፥ ይህ መሢሕ የእግዚአብሔርና የሰው ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ አምላክ ቢሆንም እንኳ ትሑት ሆኖ የእግዚአብሔርና የሰው ዘር አገልጋይ ሆነ (ማርቆስ 10፡45 ተመልከት)። በትሕትናና በመታዘዝ እስራኤልና ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር፥ እንዲሁም እርስ በርሳቸው ሊኖራቸው የሚገባ ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት ገለጠ።

21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አምላክ የሆነው ኢየሱስ፥ አገልጋይ መሆኑ የሚያስገርመው ለምንድን ነው? ለ) ኢየሱስ አገልጋያችን የሆነው በምን መንገድ ነው? ሐ) እንዴት የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆን እንደምንችል ግለጽ። መ) የሌሎች አገልጋዮች መሆን የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ምሳሌዎችን ስጥ። ሠ) የእግዚአብሔርና የሌሎች አገልጋዮች ለመሆን የሚፈቅዱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቁጥር ያነሰው ለምንድን ነው?

10. መሢሑ የሚመሠርተው መንግሥት፡- ትንቢተ ኢሳይያስ መሢሑ ስለሚመሠርተው ዘለዓለማዊ መንግሥት ብዙ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ይሰጣል። የዚህ መንግሥት ማዕከል ኢየሩሳሌም ትሆናለች። በዚህም ሰዎች ሁሉ አሕዛብም ሳይቀሩ መጥተው ለማምለክ በሚችሉበት

ሁኔታ ሰላምና ብልጽግና ይሆናል። እግዚአብሔር፥ በዚያ የዳዊት ዘር በሆነው በልጁ በኩል ይገዛል (ኢሳይያስ 24፡23፤ 33፡22፤ 43፡15፤ 44፡6 ተመልከት)። ምንም እንኳ ምሁራን ከእነዚህ ትንቢቶች መካከል ቀጥተኛ የሆኑትና ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ የቀረቡት ምን ያህሉ እንደሆኑና ስለ አፈጻጸማቸው የማይስማሙ ቢሆንም፥ እነዚህ ትንቢቶች እግዚአብሔር በዘመኑ ፍጻሜ ስለሚመሠርተው የተከበረ መንግሥት እጅግ ውብ የሆኑ መግለጫዎችን የሚሰጡ ናቸው።

22ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር ስለ እነዚህ 10 ትምህርቶች ምን እንደሚል መረዳት ለክርስቲያኖች የሚጠቅመው ለምንድን ነው?

## 3ኛ ቀን፡- ኢሳይያስ 1-6

የምንሰብከው ወንጌል በረከትንና ፍርድን በአንድነት አጠቃልሎ የያዘ ነው። ለደኅንነታቸው በኢየሱስ ለሚታመኑና ለእርሱ በመታዘዝ ለሚኖሩ ሁሉ በረከት አላቸው። በኢየሱስ በማያምኑና እርሱን በማይታዘዙት ሁሉ ላይ ደግሞ ፍርድ አለ።

23ኛ ጥያቄ፥ ለማያምን ሰው በምትመሰክርበት ጊዜ በእነዚህ በሁለቱም የወንጌል ገጽታዎች እንዴት እንደምትጠቀም አብራራ።

ይህ ትምህርት በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ተንጸባርቋል። ትንቢተ ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለሚኖሩ ሰዎች የበረከት ቃል ኪዳን የያዘ መጽሐፍ ነው። ደግሞም ከሕዝቡ ብዙዎቹ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው በሰበቡ ስለሚቀበሉት አሳዛኝ የሆነ እውነታ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።

24ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 1-6 አንብብ። እነዚህ ምዕራፎች ትላንት የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ትምህርቶች የሚያስተምሩት እንዴት ነው?

ትንቢተ ኢሳይያስ የሚጀምረው፥ የሚጠቃለለውም ፍርድን ዋና አሳቡ በማድረግ ነው። አይሁድ ሊመጣባቸው ስላለው የፍርድ ቅጣት

በማስጠንቀቅ ይጀምራል። ክፉና ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎችን በማስጠንቀቅ ይደመደማል።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 1 የሚጀምረው በፍርድ ቤት ችሎት ፊት እንዳለ ሆኖ ነው። ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ ክስ ይመሠርታል። የገባውን ቃል ኪዳን ባፈረሰው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሰማይና ምድር ጭምር ምስክር ሆነው ቀርበዋል (ዘዳግም 4፡26)። አይሁድ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ መቅመስ ጀምረው ነበር። በመንግሥት ደረጃ በአሕዛብ መሸነፍ ጀምረው ስለነበር እንደ ሰዶምና ገሞራ ለመጥፋት ደርሰው ነበር።

እግዚአብሔር አይሁድን ወደ እርሱ እንዲመጡ፥ ከእርሱ ጋር እንዲነጋገሩና የኃጢአታቸውን ይቅርታ እንዲቀበሉ ጋብዞ ነበር። ይህ ይሆን ዘንድ ግን መንገዳቸውን መለወጥ ነበረባቸው። ሥነ- ሥርዓታዊ አምልኮአቸው ዋጋ አልነበረውም። እግዚአብሔርን በእውነት ለማምለክ፥ ከእነርሱ የሚያንስ ዕድል ከገጠማቸው ሰዎች ጋር በፍትሕ መኖር ነበረባቸው።

የእግዚአብሔርን ፍርድ መቅመሳቸው የማይቀር ቢሆንም እንኳ ክፉት የሚጠፋበትና የእግዚአብሔር ሕዝብ ከአምላካቸው ጋር ለገቡት ቃል ኪዳን በመታዘዝ የሚኖሩበት ጊዜ ይመጣል። በዚያን ጊዜ የይሁዳ መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው ኢየሩሳሌም በጽድቅና በፍትሕ ትሞላለች።

25ኛ ጥያቄ፥ የኢሳይያስ ምዕራፍ 1 ዋና ዋና ትምህርቶችን ዘርዝርና ለቤተ ክርስቲያንህ በማስጠንቀቂያነት እንዴት ሊጠቅሙ እንደሚችሉ አስረዳ።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 2 የሚያተኩረው «በመጨረሻዎቹ ቀናት» ላይ ነው። በትንቢት ውስጥ ይህ ሐረግ በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ ሐረግ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሚሠራበት በማንኛውም ጊዜ ስለሚያመጣው ፍርድ ወይም በረከት የሚናገር ቢሆንም፥ ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ግን እግዚአብሔር ለዚች ምድር ያለውን ዕቅድ ሙሉ

በሙሉ ስለሚፈጽምበት የመጨረሻ ዘመን ነው። ኢሳይያስ ምዕራፍ 2 የሚጠቅሰው ስለዚሁ የመጨረሻ ዘመን ነው። ኢሳይያስ ምዕራፍ 2 በዚህ ጊዜ ስለሚፈጸሙ ሁለት ጉዳዮች ይናገራል፡-

1. የታላቅ በረከት ጊዜ (ኢሳይያስ 2፡1-5)፡- ይህ የበረከት ጊዜ እግዚአብሔር በምድር መንግሥታት ሁሉ ላይ በሚገዛበት ወቅት የሚፈጸም ነው። ሰዎች ሁሉ ከተለያዩ መንግሥታት እግዚአብሔርን ለማምለክ ይመጣሉ። እነርሱም ለእግዚአብሔር ሕግ ታዛዦች ሆነው ይኖራሉ። እርሱ ደግሞ በመካከላቸው እውነተኛና ጻድቅ ፈራጅ ይሆናል። በሕዝቦች መካከልም ዘላቂ ሰላም ይሆናል።

2. የታላቅ ፍርድ ጊዜ (ኢሳይያስ 2፡6-22)፡- የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት አይሁድ የእግዚአብሔርን ታላቅ በረከት ቀምሰውት ነበር። ብዙ ብር፥ ወርቅ፥ ፈረሶች፥ ወዘተ. ነበሯቸው። ነገር ግን ጣዖትን ማምለክና ትዕቢትን የመሰለ ከፍተኛ ክፋትም በመካከላቸው ነበረ። ስለዚህ የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ሲመጣ ክፉ ያደረጉትን ሁሉ ይቀጣል። የእግዚአብሔር ፍርድ የእርሱን ገናናነት በመግለጥ ሕዝቡ እንዲፈሩት ያደርጋል። ሰው መፍራት የሚገባው ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያስጥለው የማይችለውን ሰውን ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን ነው።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 3 የሚያተኩረው በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ኃጢአት እንዲሁም እግዚአብሔር እነርሱን በሚቀጣበት ምክንያት ላይ ነው። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ በሚመጣ ጊዜ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ከሁሉ በላይ የሚቀበሉት መሪዎች ነበሩ። በእስራኤል መሪዎች የማይኖሩበት ጊዜ ይመጣል። ለሕዝቡ መውደቅ እግዚአብሔር መሪዎችን እንዴት እንደሚወቅስ አስተውል (ኢሳይያስ 3፡12-15)። በተጨማሪም ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔር በመታዘዝ ሳይኖሩ፥ ስለ ውጫዊ ውበታቸው ብቻ ስለሚያስቡና ስለሚታበዩ ሴቶች ኃጢአት አበክሮ ይናገራል። እግዚአብሔር በውበታቸው የታበዩትን እነዚህን ሴቶች ውበታቸው ወደሚረግፍበትና ወንዶቻቸው ወደሚገደሉበት ምርኮ በማፍለስ እንደሚያዋርዳቸው ይናገራል።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 4 እንደገና ተመልሶ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅሬታዎች ለወደፊት ስለሚያገኙት ክብር ይናገራል። በዚህ ክፍል

የመሢሑ ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ስም ከሆነው «ከእግዚአብሔር ቍጥቋጥ» ጋር እንድንተዋወቅ ተደርጓል። እስራኤል ወደ ቀድሞ ክብርዋ ትመለሳለች፤ ሕዝቡም የተቀደሱ ይሆናሉ። እግዚአብሔር በምድረ-በዳ እንዳደረገው (ዘጸአት 40:34-38)፥ በመካከላቸው እንደ እሳት ዐምድና እንደ ክብር ደመና ይኖራል።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 5 እንደገና በፍርድ መሪ አሳብ ላይ ተመሥርቶ፥ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚፈርድባቸው ምክንያቶች ላይ ያተኩራል። ኢሳይያስ 5:1-7 እስራኤል ከወይን ቦታ ጋር ተነጻጽራ የቀረበችበት የፍርድ መዝሙር ነው። በእስራኤል ውስጥ በጣም ከተለመዱና ከታወቁ የእርሻ ሥራዎች አንዱ የወይን ተክል ሥራ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመግለጥ ወይንን በምሳሌነት ተጠቀመ። እግዚአብሔር የራሱን ወይን-እስራኤልን በከነዓን ምድር ተከለ፤ ጠበቃት፤ ተንከባከባትም። ነገር ግን እስራኤል የጽድቅ ፍሬ የሆነውን መታዘዝን በማፍራት ፈንታ ኮምጣጣ የሆነውን ያለመታዘዝንና የሐሰተኛ አምልኮን ፍሬ አፈራች። ስለዚህ እግዚአብሔር በወይኒቱ ላይ ይፈርዳል ያጠፋታልም።

በኢሳይያስ 5:8-30 የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጡትንና በሕዝቡ መካከል ተስፋፍተው የነበሩትን ኃጢአቶች በዝርዝር እንመለከታለን። እነርሱም እያንዳንዳቸው የ «ወዮታ» ቃል የያዙ ስድስት ኃጢአቶች ነበሩ። በድሆች ጉልበት፥ ድካምና ጥረት ያለማቋረጥ ሀብት እያካበቱ የመኖር ፍላጎት የነበራቸው ሰዎች፥ ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ባለባቸው ኃላፊነት ግድ የሌላቸውና ግብዣ በማድረግ የሚሰክሩ መሪዎች፥ በክፉትና በግፍ ደስ የሚሰኙና እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ በተናገረው ቃል ላይ የሚሳለቁ፥ እግዚአብሔር መልካም ነው ያለውን ነገር ክፉ ነው የሚሉ ወይም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆኑትን ነገሮች መልካም ነው የሚሉ፥ በጥበባቸው የሚታበዩ፥ እንደዚሁም አዘውትረው የሚሰክሩና ፍርድን የሚያጣምሙ ሰዎች ነበሩ።

ኃጢአት ቅጣትን ያመጣል። በመሆኑም እግዚአብሔር ለእርሱ ባለመታዘዝ የሚኖሩትን ሰዎች እንደሚቀጣ ይናገራል። እግዚአብሔር ታላቅና ኃያል የሆነ ባዕድ ሕዝብን በይሁዳ ሕዝብ ላይ በማስነሣት ያጠፋቸዋል።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 6 ስለ ኢሳይያስ መጠራትና ለይሁዳ ሕዝብ የእግዚአብሔር ነቢይ እንዲሆን ስለ መመረጡ ይነግረናል።

26ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ምዕራፎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ የሚመላለሱ ከሆነ ስለሚያጋጥሟቸው ነገሮች የሚያስጠነቅቁት ምንድን ነው? ለ) ሀብታቸውንና ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ ስለሚጠቀሙ ሰዎች እነዚህ ምዕራፎች የሚያቀርቡት ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ሐ) እነዚህ ምዕራፎች በመከራና በሥቃይ ጊዜያት ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ማበረታቻ የሚሆን የወደፊት ተስፋ የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው?

## 4ኛ ቀን፡ - ኢሳይያስ 7-12

ብዙውን ጊዜ አንድ ክርስቲያን ችግር ሲያጋጥመው የሚወስደው የመጀመሪያ እርምጃ ከሌላ ክርስቲያን ወይም ከጎረቤት ወይም ከወዳጅ እርዳታ መፈለግ ነው፤ ወይም ደግሞ መንግሥት ነገሮችን እንዲያቃናለት ወይም እንዲያስተካክልለት ወደ መንግሥት ፊቱን ያዞራል።

27ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ችግር አጋጥሞህ የነበረበትን ጊዜ ዘርዝር። እርዳታ ፍለጋ የሄድከው ወደ ማን ነበር? ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ችግር አጋጥሟት የነበረበትን ጊዜ ዘርዝር። እርዳታ ፍለጋ የሄደችው ወደ ማን ነበር?

ብዙ ክርስቲያኖች ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ወዲያውኑ እርዳታ ፍለጋ ወደ ሌሎች ክርስቲያኖች ወይም ወደ ዘመዶቻቸው ይሄዳሉ። እነርሱ ወይም ቤተ ክርስቲያናቸው ወደ ሕግ ነክ ችግሮች ውስጥ ከገቡ ደግሞ መንግሥት (ፍርድ ቤት) ለእነርሱ እንደሚፈርድላቸው በማሰብ ወደሚመለከተው ክፍል ይሄዳሉ። በዚህ ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አንዳችም ስሕተት ባይኖርም እንኳ አደገኛ የሆነ መንፈሳዊ ችግርን የሚያስነሣ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። እኛ ወይም ቤተ ክርስቲያናችን ችግር በሚገጥመን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለብን። በችግራችን ጊዜ መጠጊያችንና ረድኤታችን እርሱ ብቻ ሊሆን ይገባል። ረድኤት የምንፈልገው ሁልጊዜ ከሰዎች ከሆነ በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት ማደግን አንማርም፤ እግዚአብሔር ስለ እኛ ሆኖ ይሠራ ዘንድም አልፈቀድንለትም ማለት ነው።

ኢሳይያስ ከምዕራፍ 7-12 የተጻፈው የይሁዳ ሕዝብና ንጉሥ አካዝ በችግር ውስጥ በነበሩ ጊዜ ነው። የሶርያ ንጉሥ የነበረው ረአሶን የእስራኤል ንጉሥ ከነበረው ፋቁሔ ጋር በመተባበር የይሁዳን ሕዝብ ለመውጋት ዐቀዱ። ንጉሥ አካዝ ምርጫ ነበረው፤ ይኸውም፡- በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል የመጣለትን የእግዚአብሔርን ቃል በማመንና በእግዚአብሔር በመታመን ጠላቶቹን ማሸነፍና ዕቅዳቸውን ማክሸፍ ወይም ደግሞ እንደ አሦራውያን ወዳሉ ሌሎች መንግሥታት ዕርዳታ ፍለጋ መሄድ። ብዙዎቻችን ዛሬ እንደምናደርገው፥ በዚህ የችግር ጊዜ አካዝ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ መታመን አቃተው፤ ነገር ግን ወደ አሦራውያን ሄዶ ጠላቶቹን በመውጋት እንዲረዱት ጠየቀ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አሦራውያን የእርሱን መንግሥትና ሕዝብ ሙሉ በሙሉ እንደሚያጠፉ አልተገነዘበም ነበር። አካዝ በእግዚአብሔር መታመን ስላልቻለ በሕዝቡ ላይ ከፍ ያለ ችግር አመጣ።

28ኛ ጥያቄ፥ አንተ ወይም ሌላ የምታውቀው ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን በችግር ጊዜ ዕርዳታ ወይም መፍትሔ ፍለጋ ወደ አንድ ሰፍራ ሄዳችሁ፥ አስቀድሞ ከነበረው ችግር የላቀ ከባድ ችግር ይዛችሁ የተመለሳችሁበትን ሁኔታ በምሳሌነት ጥቀስ።
29ኛ ጥያቄ፥ ኢሳይያስ 7-12 አንብብ። ሀ) የኢሳይያስ ልጆች ስሞችን ከነትርጒማቸው ተናገር። ለ) እግዚአብሔር ለንጉሥ አካዝ የሰጠው ምልክት ምን ነበር? ሐ) እግዚአብሔር ለእስራኤልስ ሕዝብ (ኤፍሬም) የሰጠው ተስፋ ምን ነበር? መ) የአሦር ሕዝብ ምን ያደርግ ነበር? ሠ) ንጉሥ ይሆን ዘንድ ላለው ሕፃን የተሰጡትን የተለያዩ ስሞች ዘርዝር (ኢሳይያስ 9፡6-7)። ረ) ከዳዊት ዘር ስለሚመጣው ቅርንጫፍ ወይም ቍጥቋጥ የተሰጡትን ተስፋዎች ዘርዝር (ኢሳይያስ 11)።

ኢሳይያይስ 7-12 የተጻፈው የይሁዳ ሕዝብ በብሔራዊ ችግር ውስጥ ሳለ ነበር። የይሁዳ ሕዝብ በሶርያ (አራም) እና በእስራኤል (ኤፍሬም) ሊደመሰስ የተቃረበበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር ለኢሳይያስና ለይሁዳ ሕዝብ ስለ መሢሑ መምጣት የሚናገሩ በርካታ አስደናቂ ትንቢቶችን የሰጣቸው በዚህ ጊዜ ነበር።

በኢሳይያስ ምዕራፍ 7÷ እግዚአብሔር ኢሳይያስን ወደ አካዝ እንዲሄድና ብሔራዊ ሰቆቃ ባለበት በዚህ ጊዜ ውስጥ በጌታ ይታመን ዘንድ እንዲያበረታታው ነገረው። ኢሳይያስ የስሙ ትርጒም «ቅሬታዎቹ ይመለሳሉ» የሚለውን ልጁን ሸር-ያሹብን አስከትሎ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሄደ። ይህ የኢሳይያስ ልጅ ይህንን ስያሜ ያገኘው የይሁዳ ሕዝብ እንደሚጠፉ÷ ነገር ግን እግዚአብሔር አንድ ቀን ወደ ይሁዳ ምድር የሚመልሳቸው ቅሬታዎች እንደሚኖሩ የሚያመለክተውን የኢሳይያስን መልእክት ለማንጸባረቅ ነበር። እግዚአብሔር ለአካዝ የእስራኤልን (የኤፍሬምን) ጦር እንዳይፈራ ነገረው። (የእስራኤል ጦር ኤፍሬም በመባል የሚጠራው በእስራኤል ውስጥ ያለው ዋናው ነገድ የኤፍሬም ነገድ በመሆኑ ነው)። ይልቁንም የሶርያም ሆነ የእስራኤል መንግሥታት በ65 ዓመታት ውስጥ ሊደመሰሱ ነበር። ይህ ትንቢት የሶርያና የእስራኤል መንግሥታት በአሦራውያን ሙሉ በሙሉ በተደመሰሱባቸው በ732ና በ722 ዓ.ዓ. ተፈጽሟል።

እግዚአብሔር ይህ ትንቢት እንደሚፈጸም ለአካዝ ለማረጋገጥ ሲል እውነትነቱን የሚያሳይ ምልክት እንዲጠይቅ ፈቀደለት። ምልክት ብዙ ጊዜ ወደ ፊት የሚፈጸም ትንቢትን እርግጠኛነት ለማሳየት በቅርቡ የሚፈጸም ድርጊት ነው። አካዝ በአሦራውያን እንጂ በእግዚአብሔር መታመን ስላልፈለገ ምልክት ለመጠየቅ ሳይፈቅድ ቀረ፤ እግዚአብሔር ግን ለአካዝ ምልክትን ሰጠው። ምልክቱም አንዲት ድንግል አማኑኤል ተብሎ የሚሰየም ልጅ እንደምትወልድ ነበር።

ስለዚህ ምልክት ምሁራን የተለያየ አሳብ አላቸው። ከአዲስ ኪዳን በግልጥ እንደምንረዳው ይህ ትንቢት ልዩ በሆነ መንገድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተፈጽሞአል። ይህም የሆነው ድንግል ማርያም አምላክ የሆነውን ልጅ በመውለዷ ነው (ማቴዎስ 1፡23)። ነገር ግን ትንቢቱ የሚፈጸመው ወደፊት ስለነበረ ምልክቱ አካዝን የሚያበረታታ አልነበረም። ስለሆነም የዚህ ትንቢት አፈጻጸም በሁለት በኩል ሳይሆን አይቀርም። የመጀመሪያው÷ የተፈጸመው በኢሳይያስና በአካዝ ዘመነ መንግሥት ነው። የኢሳይያስ የመጀመሪያ ሚስት የሆነችው የሸአር-ያሹብ እናት ስለሞተች÷ ኢሳይያስ ሌላ ሴት የሚያገባበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ስለሆነም ድንግል የሆነች ሴት በማግባትና የምትወልደው ልጅ «አማኑኤል» የሚል

ስም እንዲሰጠው በማድረግ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለነበር የይሁዳ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ እንደማይጠፋ አመልክቷል። ልጁ ባደገ ጊዜ አሦራውያን ሶርያንና እስራኤልን ስላሸነፉ የሁለቱ አገሮች ዛቻ አክትሞ ነበር። ምሁራን፥ ይህ አማኑኤል የሚለው ስም «ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ» የሚል ትርጓሜ የነበረው የኢሳይያስ ሁለተኛ ልጅ ሌላ ስም ስለመሆኑ ይሁን ወይም የሌላ ልጅ ስም የተለያየ አመለካከት አላቸው።

ኢሳይያስ ስለሚመጣው ስለ አሦር መንግሥት ተነበየ። የአሦር መንግሥት ከሶርያና ከእስራኤል ጥቃት የይሁዳን መንግሥት ለጊዜው ማሳረፍ ብቻ ሳይሆን፥ በመጨረሻ በይሁዳ ሕዝብና በዳዊት ቤት ላይ ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያመጣ ኢሳይያስ ተንብዮ ነበር።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 8 ወደፊት በይሁዳና በአሦር መካከል ስለሚደረገው ጦርነት መተንበዩን ይቀጥላል። አሦር የቅጣት መሣሪያ ትሆን ዘንድ በተለይ በእግዚአብሔር የተመረጠች መሆኑን ኢሳይያስ ተናግሮ ነበር። እርሷ «የእግዚአብሔር በትር» ሆና ነበር። ይህ እንደሚፈጸም ምልክት ይሆን ዘንድ ኢሳይያስ የስሙ ትርጉም «ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ» የተባለ ሌላ ልጅ ወለደ። ይህ ልጅ፥ ይሁዳ በኃጢአት ምክንያት በአሦር መንግሥት የምትማረክና የምትበዘበዝ መሆንዋን የሚያመለክት ትንቢት ነበር። ይህ ትንቢት በሕዝቡ ዘንድ ባይወደድም፥ ሰውን ሳይሆን እርሱን እንዲፈራው እግዚአብሔር ኢሳይያስን አስጠንቅቆት ነበር (ኢሳይያስ 8፡12-13)። እጅግ አስጨናቂ በሆኑ ጊዜያት እንኳ ኢሳይያስ በእግዚአብሔር ለመታመንና ሕጉንና ምስክርነቱን ለመስማት ወሰነ (ኢሳይያስ 8፡17፥ 20)።

30ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አካዝ በእግዚአብሔር ሳይሆን፥ በአሦር ለመታመን ሲወስን ምን ነገር ተፈጸመ?
ለ) ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት እንዳለበት እግዚአብሔር ለኢሳይያስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅግ ጠቃሚ ምክር የሚሆነው እንዴት ነው? ሐ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ሊፈራ የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

በኢሳይያስ 9-10 ስለ መሢሑ የተነገሩ ትንቢቶችን ቀጥለን እናያለን። የንፍታሌም ነገድና የገሊላ ምድር እንደሚከበሩ ኢሳይያስ ይተነብያል። የንፍታሌም ነገድና የገሊላ ምድር የሚገኙት በእስራኤል ሰሜናዊ ክፍል ሲሆን፥ ብዙ ጊዜ አሕዛብ ይወሩት ነበር። ብዙ ጊዜ በአሕዛብ ቊጥጥር ሥር የሚቆይ ምድር ነበር። ኢሳይያስ ይህን ትንቢት በሚናገርበት ጊዜ፥ ይህ ክፍል የአሦር ሕዝብ ግዛት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠር ነበር። እግዚአብሔር ግን አንድ ቀን በገሊላ ልዩ የሆነ ብርሃን እንደሚበራ ተናገረ። ይህም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴዎስ 4፡15-16)። በይሁዳ ሕዝብ ዘንድ ገዥ የሚሆን ልዩ ልጅ እንደሚወለድ ተነገረ። መሢሕ ለሆነው ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጡትን ስሞች ተመልከት፡-

1. ድንቅ መካር፡- እነዚህ ሁለት ጣምራ ቃላት መሢሑ በንግሥናው ሕዝቦች የሚደነቁበትን ልዩ ተግባር እንደሚፈጽም የሚያሳዩ ናቸው።

2. ኃያል አምላክ፡- ይህ ሕፃን አምላክ ነው፤ ነገር ግን ጠላቶቹን ደምስሶ ለመግዛት የሚችል ኃያልም ነው።

3. የዘላለም አባት፡- ገዝተው እንደሚሞቱ በጥንት ዘመን እንደነበሩ ነገሥታት ሳይሆን፥ መሢሑና መንግሥቱ ለዘላለም የሚኖሩ ናቸው። እንደ አባት የሕዝቡ ጠባቂና ተንከባካቢ ነው።

4. የሰላም አለቃ፡- በዚያን ጊዜ የይሁዳ ሕዝብ ይኖሩበት እንደነበረው መሢሑ በጦርነት ጊዜ ከመግዛት ይልቅ በምድር ላይ፥ በግለሰቦች ሕይወት፥ በኅብረተሰብ፥ እንዲሁም በሀገሪቱም ሁሉ ዘንድ ሰላምን ስለሚያመጣ ግዛቱ የሰላም ይሆናል።

31ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እነዚህ የኢየሱስ ስሞች የሚያበረታቱን እንዴት ነው?
ለ) የኢየሱስን ባሕርይ የሚወክሉት እነዚህ ስሞች በችግር ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ በእርሱ ብቻ እንድንታመን የሚያበረታቱን እንዴት ነው?

የመሢሑ መንግሥት የሚከተሉት ባሕርያት ይኖሩታል፡-

1. ዘላለማዊ ነው።

2. በዳዊት ዙፋን ላይ ይቀመጣል።

3. መንግሥቱ የፍትሕና የጽድቅ መንግሥት ይሆናል።

የኢሳይያስ ምዕራፍ 9 የመጨረሻ ግማሽና የምዕራፍ 10 የመጀመሪያ ክፍል በይሁዳ ላይ በቅርብ ጊዜ ስለ ሚፈጸመው ጉዳይ በመመለስ፥ በእግዚአብሔርና በገቡት ቃል ኪዳን ላይ በማመፃቸው ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል።

ዳሩ ግን በኢሳይያስ ምዕራፍ 10 መጨረሻ እግዚአብሔር በአሦር ላይ ስለሚመጣው ቅጣትና ፍርድ አስቀድሞ ይናገራል። አሦር፥ ልዑል አምላክ ሕዝቡን ለመቅጣት የተጠቀመባት መሣሪያው ብትሆንም ስለ ጭካኔዋና ትዕቢትዋ በተራዋ እግዚአብሔር ይቀጣታል። ይህ ትንቢት የተፈጸመው ባቢሎን አሦርን በደመሰሰችበት ወቅት ነው፤ ነገር ግን በይሁዳ ቅሬታዎች ይኖራሉ።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 11 ስለሚመጣው መሢሕ ወደ መተንበይ ይመለሳል። ይህ ትንቢት በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ ከማተኮር ይልቅ በንጉሥነት ባሕርዩ ላይ ወደማተኮር ያዘነብላል። ይህ መሢሕ ከእሴይ ግንድ የወጣ በትር ወይም ቍጥቋጥ ተብሏል። ይህም መሢሑ በእግዚአብሔር ፍርድ ምክንያት ሊጠፋ ምንም ያህል ካልቀረው ከዳዊት ዘር እንዴት እንደሚመጣ የሚያሳይ ነው። (ለምሳሌ፦ የባሕር ዛፍ ከተቈረጠ በኋላ እንደገና እንደሚያቈጠቍጥ ዓይነት ነው።)

1. መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ይሆናል። ያም መንፈስ፦

ሀ) ለመሢሑ በአመራሩ ጥበብንና ማስተዋልን፥ ምክርንና ኃይልን፥ እንዲሁም እውቀትን ይሰጠዋል።

ለ) እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲመላለስ መሢሑን ይረዳዋል።

2. በእኩልነት፥ በጽድቅና በፍርድ ይበይናል።

3. ክፉዎችን (በብረት በትር) በኃይል ይቀጣል።

4. የፍጥረተ ዓለምን ተፈጥሮአዊ ሥርዓት በመለወጥ፥ የእንስሳት ዓለም እንኳ በዔደን ገነት ጊዜ እንደነበረው ዓይነት እንዲሆን ያደርጋል። እንስሳት እርስ በርሳቸው አይገዳደሉም፤ እባብም አያስፈራም።

5. ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ታውቃለች፤ ታከብረውማለች። የአይሁድ ነባር ጠላቶች የሆኑ አሦራውያን፥ ግብፃውያን፥ ኢትዮጵያውያን፥ ባቢሎናውያን፥ እንዲሁም ታዋቂ ጠላቶችና እስከ ምድር ዳር ድረስ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ ሳይቀሩ መሢሑን ያከብራሉ።

6. የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ የሆኑት አይሁድ ከተበተኑበት ስፍራ ሁሉ ወደ እስራኤል ይሰበሰባሉ።

32ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ስለ መሢሑና ስለ መንግሥቱ የተሰጡ እነዚህ የተስፋ ቃሎች በዘመናት ሁሉ የሚኖሩትን ሰዎች ፍላጎት የሚያሟሉት እንዴት ነው? ለ) ክርስቲያኖች በመከራ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ተስፋ የሚሆናቸው እንዴት ነው?

ኢሳይያስ ምዕራፍ 12 እግዚአብሔር በመሢሑ በኩል ሊሰጥ ስለገባው የበረከት ቃል ኪዳን የተሰጠ የምስጋና መዝሙር ነው። ኢሳይያስ የኖረበት ዘመን አሦራውያን ባመጡት ጥፋት ምክንያት የቱንም ያህል የጨለመ ቢሆን፥ አንድ ቀን እግዚአብሔር ፍጹም ጽድቅና ትክክለኛ ፍርድ የሞላበት ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ መንግሥት በምድር ላይ እንደሚያመጣ በማወቁ ደስ ሊሰኝና ሐሴት ሊያደርግ ቻለ።

33ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በእግዚአብሔር ፊት ስለሚኖረን የመንግሥተ ሰማያትና የዘላለም ሕይወት በረከት የተሰጠውን ተስፋ ማወቅ በችግር ጊዜ ውስጥ እንዴት ያበረታታናል? ለ) በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደፊት ስለሚያመጣው መንግሥት አሁን ለትንሽ ጊዜ እግዚአብሔርን በምስጋና ስገድለት።

5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው የስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. የጸሎት ጊዜ

3. የትምህርት ክለሳ

4. ውይይት

ሀ. 1) ትንቢተ ኢሳይያስ ከሌሎች የትንቢት መጻሕፍት የሚለየው እንዴት ነው?

2) የወደፊቱን ነገር ማወቅና መተንበይ ለእግዚአብሔር የማያስቸግረው ለምንድን ነው?

3) እግዚአብሔር ወደፊት የሚፈጸሙት ነገሮችን እንደሚቈጣጠር በጥብቅ ማመኑ ኢሳይያስ መጽሐፉን እንደጻፈው ለመቀበል የሚረዳን እንዴት ነው?

4) እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ እንደሚቈጣጠር እርግጠኛ መሆን ክርስቲያኖችን በአስቸጋሪ የመከራ ጊዜ የሚያበረታታው እንዴት ነው?

ለ. ኢሳይያስ የኖረበትን ዘመን አሁን እኛ ካለንበት ዘመን ጋር አወዳድር። 1) ከዚህ ዘመን ጋር የሚመሳሰለው በምንድን ነው?

2) ከዚህ ዘመን ጋር የሚለያየው በምንድን ነው?

ሐ. ኢሳይያስ ምዕራፍ 6ን በአንድነት አንብቡ። 1) ከዚህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ባሕርዩ ምን ለመማር እንችላለን?

2) እግዚአብሔር መሪዎችን ስለ መጥራቱ ምን እንማራለን?

3) ስለ መሪዎች አገልግሎት ምን መማር እንችላለን?

መ. 1) የትንቢተ ኢሳይያስን ዐበይት ትምህርቶች ጥቀስ።

2) እነዚህ ዐበይት ትምህርቶች ለቤተ ክርስቲያንህ ምእመናን የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው?

ሠ) ከኢሳይያስ 1-12 ባሉት ዓበይት እውነቶች ተወያዩ። 1) ቤተ ክርስቲያንህ ላለችበት ሁኔታ የሚያገለግሉ እውነቶች የትኞቹ ናቸው?

2) የትኞቹ እውነቶች ያበረታቱሃል? ለምን?

3) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን እውነቶች ማወቅና መስበክ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው?

5. ጸሎት።